
# ጸሎተ ሃይማኖት

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሦስተኛ እንደጻፉት



ዘኤልያስ ወ/ሚካኤል እንደተረጎመው

ሐምሌ 2003 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

# ጸሎተ ሃይማኖት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እንደጻፉት

ዘኤልያስ ወ/ሚካኤል እንደተረጎመው

ሐምሌ 2003 ዓ.ም


የተርጓሚው አድራሻ፡-

+ 251 912 05 32 60

ፖ.ሣ.ቁ. 23077/1000

E-mail: zealias19@yahoo.com

zw039291@gmail.com

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

## ምስጋና

- ይህን መጽሐፍ እተረጉመው ዘንድ አነሳስቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስፈፀመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፤
- መጽሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል አንብበው ገንቢ አስተያየቶችንና ማስተካከያዎችን ለለገሱኝ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካቸው፤
- በሀሳብና በሞራል ከጐኔ ሆነው የሚያበረታቱኝ ቆሞስ መልዐከ ጽዮን አባ አብርሃም ገ/ሚካኤልን እግዚአብሔር በፀጋ ይጠብቅልኝ፡፡

የእንግሊዘኛው ርዕስ፡- "The Creed"

ከ ______________________________

ለ ______________________________

# ማውጫ

ገጽ


መግቢያ ..........5
መቅድም ..........6
ምዕራፍ አንድ ..........8
- በእውነት እናምናለን: ..........8
- በአንድ አምላክ እናምናለን: ..........10
- እግዚአብሔር አብ: ..........12
- ሁሉን የፈጠረ: ..........14
- የሰማይና የምድር ፈጣሪ: ..........20
- ሰማይና ምድር: ..........21

ምዕራፍ ሁለት ..........27
- በአንድ ጌታ እናምናለን: ..........27
- ኢየሱስ ክርስቶስ: ..........29
- አንድያ ልጅ: ..........34
- ዓለም ሳይፈጠር: ..........39
- ከብርሃን የተገኘ ብርሃን: ..........40
- ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ: ..........41
- የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ: ..........44
- በባህርዩ ከአብ ጋር የሚተካከል: ..........44
- ሁሉ በእርሱ ሆነ: ..........46
- ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ: ..........47
- በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ: ..........50
- ሰው ሆነ: ..........51
- ስለእኛ ተሰቀለ: ..........52


www.ethiopianorthodox.org

- መከራን ተቀበለ:........................................56
- ተቀበረ: ........................................60
- ከሙታን ተለይቶ ተነሣ: ........................................61
- በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ:........................................66
- ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በክብር ይመጣል:........................................71
- ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም:........................................73

ምዕራፍ ሦስት........................................75

- በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን:........................................75
- የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት:........................................77
- ሕይወትን የሚሰጥ:........................................80
- ከአብ የሠረፀ: ........................................81
- እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን:........................................84
- በረከት የሚገኘው በሦስቱ አካላት በአንድነት ነው:........................................85
- በነቢያት የተነገረ: ........................................86

ምዕራፍ አራት........................................89

- ቤተክርስቲያን:........................................89
- አንዲት ቤተክርስቲያን:........................................91
- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ........................................94
- ዓለም አቀፋዊት ቤተክርስቲያን:........................................98
- ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን:........................................99

ምዕራፍ አምስት........................................101

- ኃጢአት የሚሠረይባት አንዲት ጥምቀት:........................................101
- አንዲት ጥምቀት:........................................104
- የሙታን መነሣት፣ ........................................104
- የዚህ ዓለም ፍፃሜ፣ ........................................108
- የሚመጣው ሕይወት፣ ........................................109




## መግቢያ

ጸሎተ ሃይማኖት የክርስትና እምነታችን ህልውና ነው። በዓለም ላይ ያሉ ሁሉም የክርስቲያን አብያተ ክርስተያናት አንድ አይነት እምነት አላቸው። ለዚህ እምነት ተገዢ ያልሆኑት ክርስቲያኖች ተብለው ሊጠሩ አይችሉም።

ቤተክርስቲያንም ለጸሎተ ሃይማኖት ትልቅ ዋጋ ሰጥታዋለች፤ በመሆኑም ጸሎት ለእምነታችን ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም ወሳኝ አካል በመሆኑ ይሄንኑ ጸሎተ ሃይማኖትን በቀንና በማታ ከምንጸልያቸው የጸሎት ክፍሎች መድባዋለች።

ስለዚህ ጸሎተ ሃይማኖትን ግልጽ በሆነ አቀራረብና በጥልቀት እንዲያብራራ በማሰብ ይህን መጽሐፍ ማተሙ ተገቢ ሆኖ አግኝተዋል። ይህ መጽሐፍ በስነ መለኮት ትምህርት ቤቶች በሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ስለ ሃይማኖቱ በጥልቀት ማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ በማስተማሪያነት ያገለግላል።

ጸሎተ ሃይማኖት የተለያዩ መሠረተ እምነቶችን አጠቃሎ ይዟል። ለምሳሌ:- ምስጢረ ሥላሴ፣ የእግዚብሔር ወልድ አምላክነት፣ የእግዚአብሔር መንፈስቅዱስ አምላክነት፣ ነገረሥጋዌ፣ እና ነገረ ድኅነት፣ ጥምቀት፣ ትንሣኤ እና የሚመጣው ሕይወት በጥቂቱ ይጠቀሳሉ።

ይህን መጽሐፍ የሚያጠና እና ያጠና ማንኛውም ሰው፣ በጥንት ጊዜያት ለአህዛብ ከመጠመቃቸው በፊት የተሰጡትን ትምህርቶች ያጠቃለሉ በርካታ ቁጥር ያላቸውን የእምነት ሕጎችን ያውቃል።

<u>አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ</u>



www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም

በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ የተገለፁት ያእምነት መሠረታዊ እውነታዎች ከጥንት ጊዜያት ጀምረው የኖሩ እውነቶች ናቸው። ክርስቲያኖች እነዚህን የእምነት እውነታዎች በመጀመሪያዎቹ ሦስት የትውልድ ዘመናት ኖረውባቸዋል። ከነዚህ እውነታዎች መካከል አብዛኞቹ በሐዋርያት ሕጐች ውስጥ እንዲሁም በተወሰኑት የአባቶች አባባል ውስጥ ተካተዋል። ስለ ጸሎተ ሃይማኖት እጅግ ጠቃሚው ነገር በክርስትናው ዓለም ውስጥ ያሉት ሁሉም አብያተክርስቲያናት ራሳቸው ሁላቸውም በተቀበሉት በአንድ እምነት ማመናቸው ነው። ስለዚህ ጸሎተ ሃይማኖት በዓለም ላይ ያሉ የሁሉም አብያተክርስቲያናት ተወካዮች በፈጠሩት ሃይማኖታዊ ጉባኤ (ecumenical council) አማካይነት መደንገጉ አግባብ ነው።

ጸሎተ ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ የተደነገገው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ 325 ዓ.ም. በተካሄደው የኒቅያ ጉባዔ ነው። የኒቅያ ጉባኤ የክርስቶስን አምላክነት ተቃውሞ የተነሳው የአርዮስ የክህደት ትምህርት የተወገዘበት የመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉባኤ ነው። የመንፈስቅዱስን አምላክነት የተመለከተው ክፍልም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ381ዓ.ም. ቁስጥንጥንያ ላይ በተካሄደው ጉባኤ ላይ ተጨምሯል። ይህም የሆነው የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የተቃወመው መቅዶንዮስ በተወገዘበት ጉባኤ ላይ ነው።

ሁሉም የአለም አብያተክርስቲያናት በተወሰኑ መሰረተ እምነቶች ባይስማሙም ጸሎተ ሃይማኖት በያዛቸው ሁሉም ነጥቦች ያምናሉ። በተጨማሪም በጸሎተ ሃይማኖት የማያምን ማንኛውም የእምነት ተቋም





በአጠቃላይ እንደ ክርስቲያን አይቆጠርም፤ ለምሳሌ ያህልም የይሖዋ ምስክርነት ተከታዮች እና የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት እምነት ተከታዮች ከሁለቱ ኪዳናት ውጪ (እነርሱንም ቢሆን በራሳቸው ትርጉም ብቻ ነው የሚረዷቸው) በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ በተካተቱት ሁሉም ክርስቲያኖች በሚያምኑባቸው መሰረተ እምነቶች አያምኑም።

ጸሎተ ሃይማኖት ተከታዮቹን ዋነኛ የእምነት እውነቶች አጠቃሎ በውስጡ ይዟል።

1. የእግዚአብሔር አንድነት፡- ጸሎተ ሃይማኖት በአንድ አምላክ በእውነት እናምናለን በሚል ቃል ይጀምራል።
2. ቅድስት ሥላሴ፤ አምላክነት እና የእያንዳንዳቸው ሚና፤
3. የእግዚአብሔር ሰው መሆን፤ ማስታረቅ እና ማዳን፤
4. ኃጢአትን ለማንጻት የጥምቀት አስፈላጊነት፤
5. ትንሣኤ ሙታን እና የሚመጣው ዘላለማዊ ህይወት፤
6. የክርስቶስ ለፍርድ ዳግመኛ መምጣት፤
7. አንዲት፤ ቅድስት፤ ዓለም አቀፋዊት እና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያንና ሌሎችም በቀጣዮቹ ገጾች እያንዳንዳቸው የጸሎተ ሃይማኖት ክፍሎች ይተነተናሉ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አንድ

**በእውነት እናምናለን:**

እምነት - ማመንን፣ እምነትን በአእምሮና በልብ የሚደረግ ፍፁም መቀበልን ያጠቃልላል፤ ቅዱስ ጳውሎስ «እምነትን ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥና የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» (ዕብ 11÷1) ሲል ይገልፀዋል::

ለምሳሌ:- እኛ ከምክንያታዊነት በተቃራኒው እና ከእውቀት ደረጃ በላይ ቢሆኑም በተዓምራት እናምናለን:: ተዓምራትን እግዚአብሔር ይሠራቸዋል ብሎ ከማሰብ በስተቀር አእምሮ ለነዚህ ነገሮች ምንም አይነት ማብራሪያ ማግኘት አይችልም:: ስለዚህ አንድ ሰው መረዳት ሳያስፈልገው አምኖ ይቀበላቸዋል::

በዕለታዊ ሕይወታችን ከሚያጋጥሙን ነገሮች አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለምሳሌ ውሰዱ:- ከነዚህ ግኝቶች አብዛኞቹ ተቀባይነት የሚያገኙት በተወሰኑ ሰዎች ሲሆን በአንፃሩ ብዙኃኑ አይገነዘባቸውም ወይም አይረዳቸውም:: አንድ ሰው የኤሌክትሪክ ኃይል ወይንም የስልክ መስመር ምን እንደሆነ ሳይረዳ ይችላል በአንፃሩ ሌላው አካል እነዚህን ነገሮች ማሰብ ሳይፈልግ እንዲሁ ሊቀበላቸው ይችላል:: እያንዳንዱ ሰው ኮምፒውተር እንዴት እንደሚሠራ አያውቅም እንዲሁ ግን ይቀበለዋል::

እምነት ከእውቀት ጋር ሳይሆን ከእውቀት ደረጃ በላይ ነው::
ሁላችንም ነፍስ ለሰው ሕይወት መሠረት እንደሆነች ሳናያት እናምናለን:: አእምሮም ቢሆን ነፍስ ከአንድ ሰው ከተለየች ያ ሰው እንደሚሞት ያምናል:: ነገር ግን አእምሮ ነፍስ ምን እንደሆነች ወይም አጠቃላይ





ስለነፍስ ዝርዝር ቅርጿን፣ ነገሮችን የማወቅ ችሎታዋን ወይም እጣ ፋንታዋን አያውቅም:: ይሁንና እምነት ስለነፍስ የነገረንን እንቀበላለን::

በተመሳሳይ መልኩ የሥጋ ከሞት መነሣትም አእምሮ ይህ እንዴት እንደሚፈፀም ሳያውቅ ወይም ሥጋ ወደ ትቢያ ከተቀየረ በኋላ እንዴት ወደ ሕይወት እንደሚመጣ አእምሮ ሳያውቅ ሁሉም እንደሚከናወን በእምነት የምንቀበለው ሌላው ጉዳይ ነው:: ይህ እንዴት እንደሚሆንም ልናውቅ አንችልም ይህንን ነገር በእምነት መቀበል እንጂ እንዴት እንደሚፈፀም መረዳትም አይጠቅመንም::

አእምሮ እምነት ለእኛ ያቀበለንን ይቀበላል::
እምነት ከእውቀት ወደሚበልጥ ደረጃ ከፍ ያደርገናል፤ በዚህም ጊዜም አእምሮ በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ጉዳዩን ያጠናዋል::

እነዚህ ነገሮች ከእውቀት ባሻገር በመሆናቸው እግዚአብሔር ለነቢያት እንደተናገራቸው በመንፈስ በመነሳሳት ወይም በቅዱሳት መጻሕፍት በተነገረው በማመን ብቻ ነው ልንቀበላቸው የምንችው::

በእውነት እናምናለን... ይህ ቃል እምነት ካላቸው አባቶቻችን ወይም እናቶቻችን የወረስነው እምነት ብቻ ሳይሆን በልባችን ውስጥ ባለው ጽኑ እምነት በሙሉ እውነት-በእውነት የምናምነው ነው::

እምነት ትሑት ልብ፣ ተቀባይነት እና ግልጽነት ይፈልጋል:: አንዳንድ ሰዎች ያደገ አእምሮ ይዘው የእምነት ግልጽነት ግን ይጎድላቸዋል!

አንድ ሕፃን ሁሉንም ነገር እንዲቀበል ወይም ሁሉንም ነገር እንዲቃወም የሚያደርገው የመጠራጠር ደረጃ ላይ ስላልደረሰ ያምናል:: አንድን ሕፃን



www.ethiopianorthodox.org

መጸለይ ብታስተምሩት ከእናንተ ጋር ይጸልያል እንዲሁም ጸሎቱን የሚያቀርብለት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ሳይጠይቅ እና ሳያየው በጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር ይናገራል፤ ገና አላመኑም በማለት ሕፃናትን ለማጥመቅ የሚቃወሙ ፕሮቴስታንቶች የሚደንቁኝ ለዚህ ነው። በውኑ የሕፃናቱን ያህል እምነት እነርሱ አላቸውን?

አእምሮ ከእምነት በተቃራኒው ሲያድግ በእርግጥም እንግዳ ነገር ነው። የበለጠ እያደገ ሲሄድም ተጠራጣሪ እና ተቃዋሚ ይሆናል። ስለዚህ የእምነት መሠረታውያንን በሕፃናት አእምሮ ውስጥ አስቀድሞ መትከል ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም የሕፃን እምነት ከአዋቂዎች በላይ እጅግ ኃያል እና ያደገ ነው።

በሙሉ እውቀት የተሞላ ነገር ግን እምነት የሌለው አእምሮ ፈጽሞ ድሃ ነው።

በእውነት እናምናለን....በምን?

<u>በአንድ አምላክ እናምናለን:</u>

በቅድስት ሥላሴ እናምናለን፤ አንድ አምላክ እንደሆኑም እናምናለን። ለዚህም «በአብ ስም፣ በወልድ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም...አንድ አምላክ አሜን» እንላለን።

በአንድ አምላክ ማመን የአሠርቱ ትዕዛዛት የመጀመሪያው ትዕዛዝ ነው። እግዚአብሔርም፤ «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ...ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑህ» (ዘጸ 20÷2-3) አለ። በእግዚአብሔር አንድነት ላይ የተፃፉ ሌሎች ብዙ ጥቅሶች በነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ። «ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም። ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ





እግዚአብሔር ነኝ።» (ኢሳ 43÷10-11) ዳግመኛም (ኢሳ 44÷6-9) (ኢሳ 46÷9) (ኢሳ 48÷12) ተመልከት።

አዲስ ኪዳንም እንዲሁ ስለ እግዚአብሔር አንድነት ይናገራል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው። የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ» (1ዮሐ 5÷7) ብሏል።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካምም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ፤ ይንቀጠቀጡማል።» (ያዕ 2÷19) ብሏል። ሐዋርያው ይህን ሲናገር በዕውቀት ላይ የተመሰረተ እምነት ውስጣዊውና ትክክለኛው እምነት አይደለም ማለቱ ነው። በአንድ አምላክ የማያምን እርሱ በእምነት ከዲያብሎስ ያነሰ ነው!! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው» (ማቴ 28÷19) ብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ በ...ስም አለ እንጂ...ስሞች አላለም።

በአንድ አምላክ እንጂ በብዙ አማልክት አናምንም፤

አንድ ሰው ሦስት እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። እንደ ሒሳብ ህግ 1+1+1=3 እንጂ አንድ አይሆንም፤ ነገር ግን በዚሁ በሒሳብ ህግ ደግሞ 1x1x1=1 እንጂ ሦስት አይሆንም። እግዚአብሔር ወልድ «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10÷30) አለ። እኛ በብዙ አማልክት የምናምን አይደለንም፤ ከእግዚአብሔር በቀር በሌላ አማልክት አናምንም።

ቅዱስ ሥሉስ ማለት የአማልክትን ብዛት የሚገልጽ ሳይሆን የአንድ



www.ethiopianorthodox.org

አምላክነትን ልዩ ባህርይ የሚገልጥ ነው::

እግዚአብሔር ህያው፣ አዋቂ እና መንፈስ ነው:: እግዚአብሔር በእውቀት እና በመንፈስ አንድ ሕያው አምላክ ነው:: በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው ከእውቀትና ከመንፈስ ጋር ሕያው ነው:: እነዚህ ሦስቱም አንድ ናቸው:: በተመሳሳይ መልኩ እሳት ከውስጡ ከሚወጡት ሙቀት እና ብርሃን ጋር አንድ ነው:: ዳግመኛም ጸሐይም እንዲሁም ከሙቀቷና ከብርሃኗ ጋር አንድ ናት::

እግዚአብሔር አምላክ ነው:: እግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔር እውቀት መገለጫ ወይም የእግዚአብሔር እውቀት፣ ቃልና የእግዚአብሔር ጥበብ ነው:: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: እግዚአብሔርና መንፈሱ እግዚአብሔርና እውቀቱ (አዋቂነቱ) አንድ ናቸው፣ እነዚህ ሦስቱም ደግሞ አንድ ናቸው::

<u>እግዚአብሔር አብ</u>:

ጸሎተ ሃይማኖት ከአብ ጀምሮ ስለ ቅዱስ ሥሉስ ስለ እያንዳንዳቸው አካል ነጣጥሎ አንድ በአንድ ይናገራል::

እግዚአብሔር አብ በቅዱስ ሥሉስ ውስጥ አባት በእርሱ ለሚያምኑም ሁሉ አባት ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ እንደተናገረው በማንም ያልታየ አምላክ ነው:: «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው::» (ዮሐ 1÷18) ስለዚህ አብን ማየት አንችልም በሰው ምሳሌ ሆኖ በመጣውና ሰው በሆነው ልጁ በኩል እናየዋለን እንጂ:: (ፊል 2÷7-8)





በብሉይ ኪዳን የተገለጸው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብን ያየው ማንም የለም::

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ልጆቹ ያደረገን በሐዲስ ኪዳን ብቻ ነው፣ በአንጻሩ በብሉይ ኪዳን ግን አምላክ እንጂ አባት አልነበረም በማለት በስህተት ያስባሉ፣ ነገር ግን ይህ ሃሳባቸው ስህተት ነው::

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አባት እንደሆነም አውጇል፣ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ «ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም፣ እነርሱም ዐመፁብኝ» (ኢሳ 1÷2) ሲል እንደተናገረ:: በእርሱ የሚያምኑትም አባት እንደሆነ ተናግረዋል:: «አቤቱ አንተ አባታችን ነህ እኛ ጭቃ ነን አንተም ሠሪያችን ነህ::» (ኢሳ 64÷8)

ከጥፋት ውኃ ታሪክ በፊት «የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ» (ዘፍ 6÷2) ተብሎ ተጽፏል:: የሴት ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል:: ይህም የሆነው ከቃየን ዘር ለመለየት ሲሆን የቃየን ልጆች የሰው ሴቶች ልጆች ተብለው ተጠርተዋል:: በመጽሐፈ ምሳሌ (ተግሣፅ) ውስጥም «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ::» (ምሳ 23÷26) ይላል እግዚአብሔር::

በዘመነ ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አምላክ አባትም ነበር፣ በሐዲስ ኪዳንም እንዲሁ ነበር፣ ነውም፣ ከሰው ዘር ጋር ያለው የአባትና የልጅ ግንኙነት ፈጽሞ አይለወጥም::

ይሁንና እግዚአብሔር ለእኛ ያለው አባትነት በቅዱስ ሥሉስ ውስጥ ለእግዚአብሔር ወልድ ካለው አባትነት የተለየ ነው:: ስለ አንድያ ልጅነት በምንናገርበት ርዕስ ጉዳይ ላይ ይህ ተብራርቶ ቀርቧል::



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር እንደልጆቹ የሚንከባባበንና የሚያከብረን አባት ከሆነ እኛም ደግሞ በሙሉ ፍቅር አክብሮትና መታዘዝ ልናከብረው ይገባናል::

እግዚአብሔር አባት ነው፤ የውሃና የመንፈስ ልደትን በሠጠን ጊዜም ልጆቹ አደረገን:: «ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ...» (ቲቶ 3÷5)::

እርሱ እግዚአብሔር አብ፣ ሁሉን የፈጠረ ነው::

<u>ሁሉን የፈጠረ</u>:

እግዚአብሔር አብ ሁሉንም ፍጥረት ያስተዳድራል:: ከቁጥጥሩ እና ከፈቃዱ ውጪ የሚሆን ምንም የለም:: ሰማያውያንና ምድራውያን ፍጥረቶችን ጨምሮ ሁሉም ፍጥረታት የሚታየውም ሆነ የማይታየው ሁሉም በእርሱ ቁጥጥር ስር ናቸው:: ፍጥረትም ደግሞ መላእክትንና ሰይጣናትን ያጠቃልላል::

እግዚአብሔር ከተትረፈረፈው ምህረቱ እና ፍቅሩ የተነሣ ነፃ ፈቃድን ሰጥቶናል::

ይህንን ነፃ ፈቃድ ተጠቅመን ትዕዛዛቱን መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ እንችላለን:: ሁሉም ሥራዎቻችን በእርሱ ቁጥጥር ሥር እና በመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ የተፃፉ ናቸው:: (ሚል 3÷16) እያንዳንዱን እንደየሥራው መጠን ይከፍል ዘንድ ሲመጣ ለሥራዎቻችን ዋጋ ይከፍላል:: (ማቴ 16÷27) ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር የተፈፀሙ በርካታ የቅጣት ምሳሌዎችን እንደሚገልጹት በምድር ላይ እያለንም ሊፈርድብን ይችላል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የጥፋት ውሃ ቅጣት (ዘፍ 6) ፣የሰዶምና የገሞራ ቅጣት (ዘፍ 19) ፣ የቆሬ፣ የዳታንና የአቤሮን ቅጣት (ዘኑል 16) በብዙ





መቅሰፍቶች ተመትቶ ቀይ ባሕር የሰጠመው የፈርዖን ቅጣት (ዘፀ 16) ሲሆኑ ከነዚህ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ወዳጆች ኃጢአት ሲያደርጉ እንደዳዊት የሚቀጡትም ምሳሌዎቻችን ናቸው:: (2 ሳሙ 12)

ዲያብሎስ የክፋት አምላክ ሳይሆን ሁሉን በፈጠረው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ያለ ከእግዚአብሔር ፍጡሮች መካከል አንዱ ነው::

እግዚአብሔር የዲያብሎስን እንቅስቃሴ መግታት ወይም ገደብ ማስቀመጥ ቢፈልግ እግዚአብሔር ይህንን ማድረግ ይችላል:: በጻድቁ በኢዮብ ታሪክ ውስጥ ዲያብሎስ ኢዮብን ለመፈተን የተወሰኑ ገደቦች ያሉት ፈቃድ ወስዷል:: በመጀመሪያው ፈተና እግዚአብሔር ለዲያብሎስ በኢዮብ ሃብትና ንብረት ላይ ሃይልን ሰጠው ዲያብሎስም ከዚያ ደረጃ በላይ መሄድ አልቻለም (ኢዮ 1):: በሁለተኛው ፈተና ዲያብሎስ የኢዮብን አካል እንዲነካው ፈቀደለት ሕይወቱን ግን እንዲነካው አልፈቀደለትም (ኢዮ 2÷6) ዲያብሎስም ታዘዘ::

በሌጌዎን ታሪክም አጋንንት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ እሪያዎች እንድንገባ ስደደን ብለው ለመኑት፣ እርሱም ፈቀደላቸው፣ (ማር 12÷13) ይህ ዲያብሎስ (ጋኔን) ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እሪያዎች መግባት እንደማይችል ያሳያል:: በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ሰይጣንን ሺህ ዓመት አስሮታል፤ ሺህም ዓመት ሲፈፀም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል (ራዕ 20÷2÷7)

ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው:: (ማቴ 10÷1) ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው:- ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ



www.ethiopianorthodox.org

ተገዝተውልናል አሉት:: (ሉቃ 10÷17) ዳግመኛም እባቡንና ጊንጡን እንረግጥ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቶናል (ሉቃ 10÷19) (እዚህ ላይ ጠላት የተባለው ሰይጣን ነው)::

ስለዚህ ሰይጣን ሁሉን በፈጠረው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ስለሆነ ልንፈራው አይገባም:: አንድ ሰው እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረ ከሆነ በዓለማት ላይ እነዚህ ሁሉ ችግሮችና ጥፋቶች ለምን ይከሠታሉ? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል:: ነቢዩ ኤርምያስ ተመሳሳይ ጥያቄ እንዲህ ሲል ጠይቋል:: «አቤቱ ከአንተ ጋር በተመዋገትሁ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለ ፍርድ ልናገር:: የኃጢአተኞች መንገድ ስለምን ይቃናል? በደልንስ ለሚያደርጉ ሁሉ ስለምን ደኅንነት ይሆናል?» (ኤር 12÷1) ጌዴዎንም የእግዚአብሔርን መልአክ «ጌታዬ ሆይ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን?» (መሳ 613) ብሎ ጠይቆታል::

እግዚአብሔር ከሚደርስብን ነገር የተወሰነ ዓላማ ይኖረዋል ብለን እናስባለን፤ ከሚደርስባቸው ፈተና በረከት ሊሰጣቸው ወይም የትዕግሥትን ስጦታ ሊሰጣቸው ፈልጎ ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የተወሰኑ ፈተናዎች እንዲደርሱብን ሲፈቅድ በጻድቁ ዮሴፍ ሕይወት እንደታየው በፈተናዎቻችን ውስጥ እግዚአብሔር በእርግጠኝነት መኖሩን ማወቅ አለብን::

በእግዚአብሔር ፍላጎት እና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል ልዩነት አለ:: የእግዚአብሔር ፍላጎት እስከመጨረሻው ፍፁም መልካም ነው ይሁንና ለፍጡራኑ በገደብ እንዲንቀሳቀሱ ምክንያታዊ የሆነ ኃይልን ሰጥቷቸዋል:: ሰዎች በተሳሳተ መንገድ በመጓዝ ጉዳትን በራሳቸውና በሌላው ላይ





ሊያስከትሉ ይችላሉ:: ይሁንና ይህ ሁሉ የሚከሰተው በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን በዚህ ሁሉ ጊዜ የሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ይመለከታል፣ ዋጋ ይከፍላል፣ ይቀጣል፣ ያስተካክላል፣ አንዳንድ ጊዜም ትዕግስቱን ያሳየናል::

እግዚአብሔር በክፉዎች ሥራ መካከል ጣልቃ ሊገባ እና ሊያስቆማቸው ይችላል:: ስለዚህ ለክፉዎች የተሰጠው ነፃ ፈቃድ እንዲሁ ክፍት አይደለም፤ ይልቁንም ዳዊትና ከእርሱም ጋር የነበሩት ሕዝብ በአንድ ወቅት «አቤቱ የአኪጦፌልን ምክር ስንፍና አድርገህ እንድትለውጥ እለምንሃለሁ» (2ሳሙ 15÷31) ሲል ዳዊት በጠየቀው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ነው::

«እግዚአብሔርም ብዙ ጊዜ ቅዱሳኑን ከክፉዎች ምክር ለመጠበቅ ጣልቃ ይገባል:: ስለዚህ ይህንን በማመን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ በዚያን ጊዜ፣ ሕያዋን ሳለን [illegible]ጡን ነበር፤...» ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች፤ ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን:: ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው:: (መዝ 124÷2፣7-8) ሲል ዘምሯል::

እግዚአብሔር ጭቆናን ይፈቅዳል ጨቋኞቹን ግን አይለቃቸውም:: እግዚአብሔር ለተጨቆኑት ይፈርዳል:: እግዚአብሔር ንጉሥ ሳኦል በዳዊት ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ ነገር እንዲያደርግ ፈቅዶለታል፤ ነገር ግን ሳኦል የእግዚአብሔርን ቅጣት አላመለጠም፤ እርሱ ራሱና ልጆቹ በጊልቦዓ ተራራ ተገድለዋልና:: የሳኦልንም ራስ ቆርጠው የጦር ዕቃውን ገፍፈው...ሬሳውንም በቤትሳን ቅጥር ላይ አንጠለጠሉት:: (1 ሳሙ 31÷8-10)::



www.ethiopianorthodox.org

አቤሴሎምም ደግሞ ተገቢ ያልሆነ ሥራ በአባቱ በዳዊት ላይ ሠራ፣ የእግዚአብሔርን ቅጣት እርሱም አላመለጠም:: በውጊያ ሥፍራ አቤሴሎም ራሱም ብዙ ቅርንጫፍ ባለው በታላቅ ዛፍ ተያዘ:: ኢዮአብም ሦስት ጦሮች በእጁ ወሰደ:: አቤሴሎምም ገና በዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሕያው ሳለ በልቡ ላይ ተከላቸው:: አሥሩም የኢዮአብ ጋሻ ጃግሬዎች ከበቡት አቤሴሎምንም መትተው ገደሉት:: (2 ሳሙ 18÷9-15)

እግዚአብሔር ቃየን ወንድሙን አቤልን እንዲያጠቃውና እንዲገድለው ፈቀደ:: ነገር ግን ቃየን ከቅጣት አላመለጠም:: በእግዚአብሔር የተረገመ እና በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ነበር:: (ዘፍ 4÷8-14)

ስለቤተክርስቲያን አሳዳጆች ስናነብም እንደነቃለን... የእግዚአብሔርን ቁጥጥር እና እውቀት ያመለጠ ማንም የለም...የኃያሉን አምላክ ኃይል፣ ፍርድ እና ቅጣት ያመለጠም ማንም የለም::

እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል ሥራዎችን ብቻ ሳይሆን ሃሳቦችንና ፍላጎቶችንም ይቆጣጠራል::

እግዚአብሔር ጽንስን እንኳን በእናቱ ማህፀን እያለ ይጠብቃል:: እርሱ የረቀቀውንና የገዘፈውን፣ የሚታዩትንም የማይታዩትንም ይቆጣጠራል...ስለዚህ በሚደርሱባችሁ በማናቸውም ሥቃዮች (መከራዎች) አትዘኑ:: እግዚአብሔር በእርግጠኝነት በዚህች ምድር ሳላችሁ ጣልቃ ገብቶ ትክክለኛውን ፍርድ ይፈርድላችኋል:: እርሱ ለተጨቆኑት ይፈርዳል:: እግዚአብሔር አክአብና ኤልዛቤል ኢይዝራኤላዊው ናቡቴን ስለገደሉት ቀጥቷቸዋል:: (1ነገ 2÷1)





ይሁንና እግዚአብሔር ብዙ ሥቃዮችን እና በርካታ መከራዎችን ፈተናዎችንና አደጋዎችን ይከላከላል:: እኛ ሳናውቅ እነዚህ ነገሮች ወደ እኛ ከመምጣታቸው በፊት ያቆማቸዋል::

በሚያሳዝን ሁኔታ እግዚአብሔርን ከሚታዩ ችግሮች ስላዳነን እናመሰግነዋለን እንጂ ረቂቅና በርካታ ከሆኑት ችግሮች ወደ እኛ ከመድረሳቸው በፊት ስለጠበቀን አናመሰግነውም:: እነዚህ ረቂቃን (የማይታዩ) ችግሮች የቆሙት እኮ በኃያሉ እግዚአብሔር ነው::

በእኛ ላይ እንዲደርሱ እግዚአብሔር የሚፈቅዳቸው ፈተናዎችና መከራዎች «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን::» (ሮሜ 8÷28) ወይም «ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተኛ ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደሙሉ ደስታ ቁጠሩት» (ያዕ 1÷2)

እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረ መሆኑን ካወቅህ እግዚአብሔር በአንተ ላይ የሚደርሰውን ብቻ ሳይሆን ከአንተም በሌሎች ላይ የሚደርሰውን እንደሚጠብቅ ታውቃለህ::

ሐሳቦችን ያነባል ልብህን ይፈትናል ፍላጎቶችህንና ስሜቶችህንም ያውቃል:: ለእርሱ የተሰወረ አንድም ነገር የለም:: ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ለአንዱ «ሥራህን አውቃለሁ» (ራዕ 2÷3) አለው::
ይህን ሁሉ ካወቅህ ለሠራኸት ለእያንዳንዷ የኃጢአት ሥራ ወይም እግዚአብሔር በሚያውቀው በውስጥህ ባለው በእያንዳንዱ ሃሳብህ ሃፍረት ይሠማሃል::

ሁሉን የፈጠረ አምላክ፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ፊት ሃፍረት ይሰማሃል::

<u>የሰማይና የምድር ፈጣሪ</u>:

«ፈጣሪ» የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ብቻ ባሕርይ ነው:: ከምንም የሚፈጥር እርሱ ነው::

የሰው አእምሮ ሊደርስበት የሚችለው እጅግ ረቂቁ ደረጃ ሠሪ መሆን እንጂ ፈጣሪ መሆን አይደለም::

በእርግጥም እጅግ ከፍተኛ የተባለውን ጥበብ እና እውቀት ተጠቅሞ የጠፈር መንኮራኩር ሠርቶ ጨረቃ ላይ የደረሰው በቴክኖሎጂም ተራቅቆ እጅግ ታላቅ ወደተባለው ደረጃ የደረሰው ሰው ሠሪ እንጂ ፈጽሞ ፈጣሪ አይደለም:: ሰው ያገኘውና የሚያገኘው ማንኛውም ግኝት በእግዚአብሔር ከተፈጠረው ቁስ የተሠራና የሚሠራ ነው::

ሁሉንም ነገሮች የፈጠረው እግዚአብሔር መሆኑን ስናረጋግጥ መለኮትነቱን በትክክል እናረጋግጣለን ምክንያቱም ፈጣሪ እግዚአብሔር እንጂ ማንም አይደለም::

ነገር ግን ይህቺን ዓለም ማን ፈጠራት? (ዘፍ 1÷2) እግዚአብሔር አብ ነው ወይስ እግዚአብሔር ወልድ? እግዚአብሔር አብ ሁሉንም ነገር በልጁ በእግዚአብሔር ወልድ በኩል' ፈጠረ::

እግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔር ቃልና አዕምሮ የእግዚአብሔርም ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ ስለሆነ (1 ቆሮ 1÷23-24) እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በአእምሮው በቃሉ (በመናገር) በጥበቡ ወይም በሌላ አባባል በልጁ ፈጥሮአል:: «ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ» (ዕብ 1÷2) «ሁሉ





በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል::» (ቆላ1÷16) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ልጁ የተናገረውም ይህ ነው::

ቅዱስ ዮሐንስም በራሱ በተጻፈው ወንጌሉ መጀመሪያ ላይ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» (ዮሐ 1÷3) ብሏል::

አንድ ችግር ቢገጥምህ እና መፍትሔ ብታገኝለት መፍትሄ ያበጀህለት አንተ ነህ ወይስ ያንተ አእምሮ? የፈታኸው አንተ፣ የፈታው አእምሮህ፣ እናም አንተ ከአእምሮህ ጋር ሆነህ መፍትሔ ሰጠኸው::

ሁሉንም ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ሁሉም ነገር በእርሱ ኃይል ውስጥ ነው በእርግጥም ከምንም ነገር የሚፈጥረው እግዚአብሔር ከሞትም ያስነሳ ዘንድ ይችላል::

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይይንና ምድርን ፈጠረ:: (ዘፍ 1÷1)

<u>ሰማይና ምድር</u>:

ሰማይ ማለት በስነ-ልሳን ትርጉም መሠረት እይታችን ሊደርስበት የሚችለው የከፍታ መጠን ነው ሲል ያስቀምጠዋል:: እዚህ ላይ ሊደንቀን የሚገባው አንድ ሰማይ ወይም ብዙ ሰማያት ካሉ ነው:: (በማቴዎስ 6÷9) «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ» ተብሎ መገለጹ ለዚህ ማሳያ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ መነጠቁንና (2 ቆሮ 12÷2) ይህም ሰማይ ገነት መሆኑን (2 ቆሮ 12÷4) ይነግረናል:: ሦስተኛው ሰማይ ገነት ከሆነ አንደኛውና ሁለተኛው ሰማይ ምንድር ነው?

የመጀመሪያው ሰማይ፤ ምድርን የከበባት አየር ነው:: እርሱም አዕዋፋት



www.ethiopianorthodox.org

የሚበሩበትና የእእዋፋት ሰማይ ብለን የምንጠራው ነው… ወይ ሰማይ እንደሚበርር እንደ ንስር ለራሱ ክንፍ ያበጃልና…(ምሳ 2÷35) ተብሎ እንደተጻፈ:: በሰማይ ላይ የሚበሩ አውሮፕላኖችም የሚጓዙት በዚህ ሰማይ ላይ ነው::

ሁለተኛው ሰማይ፤ ጸሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ጋላክሲ፣ እና ሁሉም ፕላኔቶች የሚገኙበት ሰማይ ነው፤ ወደ ፀሐይ የሚቀርብ ምንም ዓይነት አውሮፕላን የለም ቢቀርብም ደግሞ ይቃጠላል:: መንኮራኩሮች ጨረቃ ላይ ማረፋቸው (መድረሳቸው) እርግጥ ነው:: ነገር ግን አብዛኞቹ የዚህ ሰማይ ክፍሎች በሰዎች ግኘት አልተደረሰባቸውም:: ስለ ከዋዋብት ስለተወርዋሪ ኮከቦች እና ስለ ከዋክብት ክምችት የሚነገረው ወሬ እጅግ አስደናቂ እና እንግዳ ነው፤ በዘርፉ የተጠናውና የታወቀው ጥቂት ቢሆንም::

ከነዚህ ሦስት ሰማያት በላይ «ሰማየ ሰማያት» ይገኛል::
በዚህ በሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ዙፋን ይገኛል፤ ስለዚህ ሰማይም ጌታችን ሲያስጠነቅቀን «ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና::» (ማቴ 5÷34) ብሎናል:: ኒቆዲሞስም ስለዚህ ሰማይ «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው::» (ዮሐ 3÷13) ብሏል::

ኤልያስ ወደ ሰማይ አርጓል፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ብቻ ወደተገባው ወደዚህ «ሰማየ ሰማያት» አይደለም ያረገው::

ንጉስ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ባከበረበት ዕለት በጸለየው ጸሎቱ ውስጥ ይህን «ሰማየ ሰማያት» ገልጾታል:: «እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ!» (1 ነገ 827) ሲል ተናግሯል:: ዳግመኛም ሰማየ ሰማያትን





በዳዊት መዝሙር ውስጥ ከነቢዩ ዳዊት ጋር «እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት በአርያም አመስግኑት… ሰማየ ሰማያት አመስግኑት» (መዝ 148÷1-4) በሚለው መዝሙር እንገልጸዋለን::

ይሁንና ከከፍታቸውና ከርቀታቸው የተነሣ ሁሉም ሰማያት "ሰማይ" ተብለው ይጠራሉ፡፡ በአስሩ ትእዛዛት ውስጥ በሰባተኛው ቀን ስላለው እረፍት "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይና ምድርን ባህርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና" (ዘፀ 20፡11) ተብሏል፡፡ "ፈጠረ" የሚለው ቃል የተመረጠው እግዚአብሔር አስቀድሞ ነገሮችን ከፈጠረ በኋላ ከፈጠራቸው ከነዚህ ነገሮች የምናያቸውን ሰማያትና የምንኖርባትን ምድር ስለፈጠረ ነው፡፡

"እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" የሚለው ዓረፍተ ነገር በነዚህም ላይ የሚኖሩትንም ፈጠረ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰማይን ሁሉንም መላእክትና ሰማያዊ ሃይላትን በየማዕረጋቸው መላእክት፣ ሊቃነ መላእክት፣ ወይም ጌትነት፣ ወይም አለቅነት፣ ወይንም ሥልጣናት ቢሆኑ (ቈላ 1፡16) ሱራፌልም ሆኑ ሊቆጠሩ የማይችሉ ሰማያዊ ፍጥረታትንም ቢሆን ፈጥሯል፡፡

ምድርንም በውስጧ ካሉት ሁሉ ጋር ፈጥሯታል፡፡ የሚታዩትና የማይታዩትን ሁሉንም ነገሮች ፈጥሮአል (ቈላ 1፡16) "የሚታዩ" የሚለውን ቃል ምንነት እንዲሁ መረዳት እንችላለን፤ ነገር ግን "የማይታዩት" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

የማይታዩት፤
ይህ ማለት ቁሳዊ ነገሮች የሆኑትን ብቻ በሚያየው ሰብአዊ ስሜቶቻችን



www.ethiopianorthodox.org

ልናያቸው የማንችላቸው እና ቁሳዊ ነገሮች ያልሆኑና ሊታዩ የማይችሉት ናቸው ማለት ነው፡፡

1. ለምሳሌ ነፍሳት (መናፍስት) ከማይታዩ ነገሮች መካከል ናቸው፡፡

መላእክትን ጨምሮ መናፍስት (መዝ 104፡4) እና ብዙዎቹ በዙሪያችን ያሉ ነገር ግን እኛ የማናያቸው ከዚህ ይመደባሉ፡፡ እንደ መልአክ ቅርፅን ሲይዝ እናየዋለን ነገር ግን መንፈስ እንደመሆኑ ልናየው አንችልም፡፡ ለዲያብሎም (ለአጋንንትም) እንዲሁ ማለት ይቻላል ምክንያቱም ርኩሳን መናፍስት ቢሆኑም መናፍስት ናቸው፡፡ (ማቴ 10፡1) እነዚህ መናፍስት ይዋጉናል ነገር ግን አናያቸውም፡፡ ዲያብሎስ የተወሰነ ቅርፅ ሲይዝ ብቻ በዚያ ቅርፅ የሚታይ ይሆናል ነገር ግን መንፈስ በሆነበት በዋናው ተፈጥሮው ማየት አንችልም፡፡

አንተም ሰብአዊ ፍጡር እንደመሆንህ የሚታይ አካል እና የማይታይ ነፍስ አለህ ይህቺን ነፍስም ከሥጋ በምትለይበት በሞት ጊዜ ማየት አንችልም የተወሰኑ ቅዱሳን ነፍሳት በሚገለጡልን ጊዜ (ለምሳሌ በተአምር) ያ ቅዱስ የእኛ ስሜቶች ሊቀበሉት የሚችሉትን ቅርፅ ይዞ ይመጣል፡፡

2. በተወሰነ መሣሪያ ካልሆነ በስተቀር በአይናችን ልናያቸው የማንችላቸው እጅግ ደቃቅ ወይም እጅግ ሩቅ የሆኑ ነገሮችም አሉ፡፡

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን በማይክሮስኮፕ ወይም በሌላ መሣሪያ ካልሆነ በስተቀር በባዶ አይናችን ልናያቸው የማንችላቸው ረቂቅ ተሕዋስያን





ናቸው ልናያቸው ባለመቻላችን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ያለበለዚያ መኖር አንችልም ነበር፤ በተለይም በተበከለ አካባቢ እና አየር ውስጥ መኖር ያዳግተን ነበር፡፡ እነርሱን ሳናይ መኖራችን እድለኞች ነን፡፡

ሌሎች አንዳንድ ነገሮች ደግሞ እጅግ ሩቅ ከመሆናቸው አንጻር የማይታዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ሊታዩ የሚችሉት በቴሌስኮፕ ብቻ ነው፡፡ በሰማይ ላይ የሚኖሩ አካላት ለዚህ ምሳሌ ይሆናሉ፤ ነገር ግን የጠፈር ተመራማሪዎች በጥንት ዘመን የማይታዩ የነበሩትን እነዚህን ነገሮች በአሁኑ ዘመን ማየት ችለዋል፡፡ ይሁንና የማይታዩ ነገሮች ተብለው ከተከፈሉት ከነዚህ ዝርዝር ነገሮች ሳተላይት እና መንኮራኩሮች ሊያዩአቸው የቻሉአቸው እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑትን የሰማይ አካላት ብቻ ነው፡፡

3. በመደበቃቸው ምክንያት በአሁኑ ወቅት የማይታዩ ሌሎች ነገሮችም አሉ፤ ነገር ግን ከነዚህ ጥቂቶቹ በፍለጋና በምርምር መገኘት ችለዋል፡፡

በምድር ውስጥ ያሉትን ብረቶች ለምሳሌ ውሰዱ፤ ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት በተለያዩ ፍለጋዎችና በቁፋሮ መታየት ችለዋል፡፡ ስለዚህ ከከርሠ ምድር ውስጥ ከመገኘታቸው አስቀድሞ የማይታዩ የነበሩትን ወርቅ፣ መዳብ፣ ማግኒዥየም፣ አልማዝ እና ሌሎችንም መሰል ብረቶች ማግኘት ችለናል፡፡

በተጨማሪም ነዳጅ እና የተፈጥሮ ጋዝ እንዲሁም በሰው እጅ ያሉትና በአሁኑ ወቅት የሚታዩ የሆኑት በጥልቅ ባህር ውስጥ ያሉ ሃብቶችም መገኘት ችለዋል፡፡ ከዚያም በላይ የማይታዩ ከሆኑት ከነዚሁ ምድቦች



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ በሰው አካል ውስጥ የማይታዩ የነበሩ ነገሮች በጨረር፣ በስካን፣ በራጅ እና በሌሎችም የሕክምና መሳሪያዎች የሚታዩ ሆነዋል፡፡

4. በሰው ተፈጥሮ ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጣቸው ባህርያት አሉ፤

እነዚህ ባህርያት የማይታዩ ቢሆኑም ግን በድርጊቶቻቸው ይገለጣሉ፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው የማይታየው አእምሮ ነው፡፡ ነገር ግን ድርጊቱ ይታያል በዚህም ተለይቶ ይታወቃል፡፡ ህሊናም እንዲሁ የማይታይ ሲሆን ሥራው ግን በግልጽ ይታያል፡፡

5. ከእግዚአብሔር ለሰው የተሠጡት ሥጦታዎችም አሉ፡፡

ሥጦታ ሊታይ አይችልም ድርጊቱ ግን ይታያል፡፡ ከዚህም ባሻገር እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሰዎች ሊታይ የማይችል ጥበብን ወይም እምነትን ሊሰጥ ይችላል (1 ቆሮ 12) ነገር ግን መኖራቸውን የሚገልፀውን ሥራቸውን ማየት እንችላለን፡፡

እዚህ ላይ በእግዚአብሔር አብ ላይ የተተነተነውን የጸሎተ ሃይማኖት ክፍል እንፈጽማለን፡፡





## ምዕራፍ ሁለት

በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን

በአንድ ጌታ እናምናለን:

ጌታ የሚለው ቃል «አለቃ» እና «እግዚአብሔር» ማለት ሲሆን በጸሎታችን ውስጥ «ጌታ ሆይ» ስንል «እግዚአብሔር ሆይ» ማለታችን ነው::

በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ «ጌታ» የሚለው ቃል «እግዚአብሔር» ለማለት የሚያገለግል ነው::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አምላክነቱን ለማመልከት «ጌታ» ተብሎ ተጠርቷል::

ለምሳሌ: ስለአስጨናቂዋ (ስለአስፈሪዋ) የፍርድ ቀን ሲናገር «በዚያ ቀን ብዙዎች:- ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን?... በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል:: የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባችዋለሁ::» (ማቴ 7÷22፣23) አለ::

ይኼው «ጌታ» የሚለው ቃል በማቴ (25÷37፣44) እንደተጠቀሰው ስለመጨረሻው ፍርድ ለመናገርም ጥቅም ላይ ውሏል፤ በክብር ዙፋኑ ላይ ለፍርድ በሚቀመጥበት ጊዜ በዚህ ስም ይጠራልና (ማቴ 25÷31)፤ ቅዱስ እስጢፋኖስም በተወገረበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ በዚህ ስም ጠርቶታልና (ሐዋ 7÷59)፤



www.ethiopianorthodox.org

«ጌታ» የሚለው መጠሪያ ስለመለኮቱ በሚነገርበት ጊዜም ይህን ለማስገንዘብ ያገለግላል:: ሐዋርያት «...ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን:: (1 ቆሮ 8÷6) ብለዋልና::

ዳግመኛም «የሰንበት ጌታ» (ማቴ 128) እና «የክብር ጌታ» (1 ቆሮ 2÷8) ተብሎ ተጠርቷል:: «ጌታ» የሚለው መጠሪያ የኢየሱስ ክርስቶስን ተአምራት ለማመልከት የሚያገለግል ነው::

ይህን በተመለከተ ሊያስረግጡ ከሚችሉት ውብ ማስረጃዎች መካከል አንዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራው «ጌታ» ተብሎ ብቻ ሳይሆን «የጌቶች ጌታ» ተብሎም ተጠርቷል (ራዕ 19÷16)

ይህ መጠሪያ (በራዕ 17÷4) ውስጥም «የጌቶች ጌታ እና የነገሥታት ንጉሥ» ተብሎ ተደግሟል:: ይህም በዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ «እንግዲህ አምላካችሁ እግዘአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶች ጌታ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም» (ዘዳ 10÷17) ተብሎ እንደተገለፀው ይህ መጠሪያ ለአምላክ ብቻ የተሰጠ ነው::

«አምላክ» ከሚለው ይልቅ «ጌታ» የሚለውን ቃል መጠቀም ኢየሱስ ክርስቶስ በደረጃ (በክብር) ከአብ ያነሰ ነው ለማለት ነው ብሎ ማንም ሰው እንዳያስብ ያስፈልጋል::

ምክንያቱም:-

1. ሁለቱም መጠሪያዎች በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥተውታል «በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ





እናምናለን፤... ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ» ይላልና:: ይህ ቃል ቅዱስ ቶማስ ከትንሣኤ በኋላ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ያስታውሰናል፤ «ጌታዬ አምላኬም» (ዮሐ 20÷28) የሚለውን::

2. እያንዳንዳቸው ሦስቱ አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ «ጌታ» ተብለው ተጠርተዋል:: ስለ እግዚአብሔር አብ «ንጉሡም ዳዊት ገባ በእግዚአብሔርም ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ::...አቤቱ ይህን ታላቅ ነገር ሁሉ ታስታውቀው ዘንድ ስለባሪያህ እንደልብህም ይህን ተአምራት ሁሉ አድርገሃል::...አቤቱ እንደ አንተ ያለ የለም በጆሮአችንም እንደሰማን ሁሉ ከአንተ በቀር አምላክ የለም:: «(1 ዜና መዋ. 17÷16፣19፣20) ተብሏል:: ስለ ንጉሥ ሳኦልም የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሠቃየው:: (1 ሳሙ 16÷14) ተብሎ ተጽፏል:: (ኢሳ 61÷1ንም ተመልከት)
መንፈስ ቅዱስም በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ «ሕይወትን የሚሰጥ ጌታ» ተብሎ ተገልጿል::

3. «አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን» የሚለው አረፍተ ነገር በአንድ አምላክ በቅድስት ሥላሴ የምናምን መሆናችንን ግልጽ ያደርገዋል::

<u>ኢየሱስ ክርስቶስ</u>:

«ኢየሱስ» የሚለው ቃል «አዳኝ» ማለት ነው:: ልደቱን በማወጅ «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ::» (ማቴ 1÷21) ተብሎ ተጽፏል::



www.ethiopianorthodox.org

«ክርስቶስ» የሚለው ቃል በቁሙ ቃል በቃል ሲፈታ የተቀባ ማለት ሲሆን ይህም እንደ ንጉሥ፣ ካህን፣ እና ነቢይ የሚፈጽመውን አገልግሎቱን የሚጠቁም ነው:: ኢሳይያስ በትንቢቱ ስለ እርሱ ሲናገር «የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፤ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል::» (ኢሳ 61÷1) አለ::

«ክርስቶስ» የሚለውን ትርጉም የሚይዘው ቃል (የተቀባ) በነቢያት አማካይነት ሰውየው ካህንም ሆነ ንጉሥ ወይም ነቢይ በቅዱስ ዘይት ለተቀባ ሁሉ የሚሰጥ ስም ነበር::

ታላቁ ካህን አሮን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት በነቢዩ ሙሴ ካህን ሆኖ ተቀብቶ ነበር፤ «የተቀደሰውንም ልብስ አሮንን ታለብሰዋለህ፤ በክህነትም ያገለግለኝ ዘንድ ቀብተህ ትቀድሰዋለህ:: ልጆቹንም አቅርበህ ሸሚዞችን ታለብሳቸዋለህ፤ በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አባታቸውን እንደቀባህ ትቀባቸዋለህ፤» (ዘጸ 40÷13-15):: «ሙሴ ከቅብዓቱም ዘይት በአሮን ራስ ላይ አፈሰሰ ይቀድሰውም ዘንድ ቀባው» (ዘሌ 8÷12)

ሳሙኤል ንጉሥ ሳኦልን እንደቀባውና የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ እንዳደረበት (1ሳሙ 10÷1፣10) እንዲሁም ንጉሥ ዳዊትን እንደቀባውና የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ እንዳደረበት ሁሉ (1ሳሙ 16÷13) ነገሥታትም በተቀደሰ ዘይት ይቀባሉ::





ለነቢያት መቀባት ምሳሌ የሚሆነን እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤልያስ ያዘዘው ትዕዛዝ ነው፤ «በፈንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ...የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው::» (1 ነገ. 19÷16) ይህም ሆነ:: እነዚያ የተቀቡት ሁሉ የክርስቶስ ጌቶች ነበሩ::

ንጉሥ ሳኦል ዳዊትን ባሣደደውና ሊገድለው በፈለገ ጊዜ ሳኦል በዳዊት እጆች ሥር ወደቀ፤ የዳዊት ሰዎችም ዳዊት ሳኦልን እንዲገድለው ቢመክሩትም ዳዊት ግን ይህንን በመቃወም ለሰዎቹ «እግዚአብሔር የቀባው ነውና እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው አላቸው» (1 ሳሙ 24÷6)::

እግዚአብሔር አምላክ ለእርሱ የቀባቸውን ጠርቷቸዋል፤ ስለ እነርሱም «የቀባኋቸውን አትዳስሱ በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ» (መዝ 105÷15) ብሏል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተም፤ እርሱ እንደሌሎቹ የተቀባ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ሌሎቹ እርሱን ለመጥራት እንደተጠቀሙበት «ክርስቶስ» ወይም «መሲሕ» ነው::

ይህም ሳምራዊቷ ሴት ለርሱ በተናገረችው ቃል ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል:: «ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል» ባለችው ጊዜ እርሱም «የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ» አላት:: (ዮሐ 4÷25፣26) ሴቲቱም ለከተማዋ ሰዎች፤ «ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?» (ዮሐ



www.ethiopianorthodox.org

4÷29) አለች:: ከዚህ ሁሉ በኋላ ሴቲቱንም:- «እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን» (ዮሐ 4÷42) ይሉአት ነበር::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀቡት ሁሉ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ከጓደኞቹ ይልቅ በደስታ ዘይት የተቀባ ነው:: (ዕብ 1÷9):: ከዚህ ሁሉ ባሻገር በእርሱ ውስጥ የተቀቡት በተናጠል የሚያገኙአቸው ሦስቱም አገልግሎቶች አሉ፤ ምክንያቱም እርሱ ንጉሥ ካህን እና ነቢይ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜና ከዚህም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው::

አይሁድ ክርስቶስ የሚባል መሲሕ ይጠብቁ ስለነበር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማረጋገጥ በሌሎች ወንጌሎች ያልተገለፁ የተወሰኑ ተአምራትን አካቶ ጽፏል::

በወንጌሉ መጨረሻ ላይ ቅዱስ ዮሐንስ፤ «ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል» (ዮሐ 20÷30-31) ሲል ጽፏል:: በእርግጥም ይህ ክርስቶስ የሁሉም የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችና ምልክቶች ማዕከል ነው::

ሊታወስ የሚገባው:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጌቴሴማኒ የጸሎት ሥፍራ ከመሄዱ በፊት ከአባቱ ጋር ረዥም ንግግር ካደረገበት ዕለት በስተቀር ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ አልጠራም (ዮሐ 17÷3)፤ ነገር ግን አባቶቻችን ሐዋርያት ስለ እርሱ ሲናገሩ ይህን ስም ደጋግመው





ጠርተውታል:: በ(ሮሜ 1÷3) «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ፣በ(2ቆሮ 13÷14) «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፤ የእግዚአብሔርም ፍቅር፤ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» እንዲሁም በ(ሮሜ 16÷27) «ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን:: በመጨረሻም በ(2 ቆሮ 1÷1) «የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ» ሲሉ ጠርተውታል:: እንዲሁም ብዙ ብዙ ሌሎች ሊቆጠሩ የማይችሉ ምሳሌዎች አሉ::

አንዳንድ ሰዎች የጌታን አምላክነቱን፣ ክብሩን፣ ጌትነቱን እና ክርስቶስ መሆኑን በመዘንጋት «ኢየሱስ» ብቻ ብለው መጥራታቸው እንግዳ ነገር ነው::

ሐዋርያት ግን ይህን መገለጫውን «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» በማለት ደጋግመው ይጠቀሙበታል፤ እኛም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ ስንጀምር «ጌታችን፣ አምላካችን፣ መድኃኒታችንና የሁላችንም ንጉሥ የሆንህ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ለዘላለም ላንተ ይሁን፤ አሜን» እንላለን:: ስለዚህ ለጌታ ክብር ስንል ኢየሱስ የሚለውን ስም ብቻውን አንጠቀም::

ከዚህ ቀጥለን:-
«የአብ አንድያ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤»
የሚለውን የጸሎተ ሃይማኖት ክፍል እንቀጥላለን::



www.ethiopianorthodox.org

<u>አንድያ ልጅ፡</u>

«አንድያ ልጅ» የሚለው አገላለጽ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ከኛ የተለየ ልጅነት ያለው መሆኑን ለይቶ ለማስቀመጥ ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ባህርይ፣ ህልውና እና መለኮትነት ያለው የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ ብቻ ነውና::

የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ የሚለው አገላለጽ ቀጥለው ባሉት ጥቅሶች ላይ ተብራርቶ ተገልጿል::

(ዮሐ 1÷18)፤ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው:: ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን እንድናውቀው አደረገን ማለት ነው፤ እርሱ ራሱ «እኔን ያየ አብን አየ፤» (ዮሐ 14÷9) ብሏልና::

(ዮሐ 3÷16)፤ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::»

(ዮሐ 3÷18)፤ «በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል::»

(ዮሐ 4÷19)፤ «በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና::»

(ዮሐ 1÷14)፤ «ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ





አደረ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን»::

አንድያ ልጅ የሚለው አገላለጽ ኢየሱስ ክርስቶስን ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ባህርይ ባይኖራቸውም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ከተጠሩት ከሰዎች የተለየ ያደርገዋል::

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን ይህ ማለትም ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ እንደተናገረው አማኞች ማለት ነው: «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::» (ዮሐ 1÷12) ቅዱስ ዮሐንስ «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ» (1 ዮሐ 3÷1) እንዳለው እግዚአብሔር ለኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ልጆቹ አድርጎ ጠራን:: እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እንደ ልጆቹ እንሆን ዘንድ ጠርቶናል፤ «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ 4÷4፣5)

እኛ የእግዚአብሔር የባህርዩ እና የሕልውናው ልጆች አይደለንም:: የእግዚአብሔር ብቸኛው ባህርዩ ሕልውናው እና መለኮቱ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ስለዚህም «የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ ይጠራል::

«ልጅ» የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል «አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል:: በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን



www.ethiopianorthodox.org

አያይም::» (ዮሐ 3÷35፣36) ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ «ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም::» (ዮሐ 5÷22፣23)

«አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል::» (ዮሐ 5÷21):: እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች የወልድን መለኮትነት በግልፅ ያመለክታሉ::

የወልድ መለኮትነት ጌታችን ለአይሁድ በተናገራቸው ቃላት ውስጥም በግልፅ ተቀምጧል:: እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ::» (ዮሐ 8÷36)፤ ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም::» (1 ዮሐ 5÷12):: ጌታም ስለራሱ ሲናገር «ሁሉ ከአባቴ ዘንድ እንደሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም» አለ:: (ሉቃ 10÷22)

«የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ለማመልከት የሚያገለግል ነው::

ይህም በ(1 ዮሐ 5÷12) እና ጌታችን እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በጠየቀው ጥያቄ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል «አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?» አለው:: እርሱም መልሶ:- ጌታ ሆይ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ:: ኢየሱስም:- አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው:: እርሱም «ጌታ ሆይ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም::» (ዮሐ 9÷35-38):: ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ሊታመንበትና ሊሰገድለት ይገባዋል፤ ምክንያቱም እርሱ እንደሌሎቹ አማኞች ተራ የእግዚአብሔር





ልጅ ሳይሆን የባህርይ ልጁ እና አንድያ ልጁ ነው:: ሁሉም ሰው ከዚህ ትርጉም በመነሳት ለእግዚአብሔር የተገባ ልጅ መሆኑን ይገነዘባል::

ስቅለቱን ተከትለው በተከሰቱት ተአምሮች «የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተናወጠች፤ ዓለቶችም ተሰነጠቁ...የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው:- ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ::» (ማቴ 27÷51-54) ይህን ማለታቸው እርሱ እንደሌሎች ሰዎች ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ ወይም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነበር ማለታቸው ነው::

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን:- «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ:: ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ:- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ:: እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» (ማቴ 16÷13-18) ሲል ባረከው::

ዲያብሎስ እንኳን «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን ቃል ትርጉም ያውቃል:: ዲያብሎስ ይህ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ የሚባለውን ተራውን ምዕመን እንደማያመለክት ያውቃል:: ነገር ግን ተአምራትን ለማድረግ ሃይል ያለውን ልዩ ልጅ እንደሚያመለክት ስለሚያውቅ ስለእርሱ «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል



www.ethiopianorthodox.org

አለው::» (ማቴ 4÷3)

የዲያብሎስ ተከታዮችም ደግሞ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን ቃል ተአምራዊና መለኮታዊ ትርጉም ያውቁ ስለነበር በስቅለት ጊዜ «የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ» አሉት:: (ማቴ 27÷40)

ኢየሱስን በያዙት የሸንጎ አባላት አእምሮም ውስጥ ይህ እውነት ነበር:: ጌታችን በተያዘበት ወቅት የካህናት አለቆች፣ ሽማግሎች፣ ሸንጎውም ሁሉ በተሰበሰቡበት ሊቀካህናቱ:- «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ» አለው:: (ማቴ 26÷59-63) ኢየሱስም «አንተ አልህ» ባለው ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀዶ:- ተሳድቦአል እንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ስለምን ያስፈልጉናል? አለ:: (ማቴ 27÷65)

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማመን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ እንደሆነ ማመን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ባህርያትም ደግሞ አሉት::

የእግዚአብሔር ልጅነት ዘላለማዊ ነው፤ ከተወሰነ ጊዜ ጋር የተያያዘ አይደለም በጸሎተ ሃይማኖት [ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር የነበረ የአብ አንድያ ልጅ] እንደምንለው በተወሰነ ጊዜ ላይ የእግዚአብሔር ልጅነት እንደተገባቸው እንደሰዎች ከተወሰነ ጊዜ ጋር የተያያዘ አይደለም፤ የጂሆባ እምነት ተከታዮችና አርዮሳውያን እንደሚሉት ለመታዘዙ እንደሽልማት ያገኘው ወይም በጥምቀቱ ጊዜ ብቻ ያገኘውም አይደለም::

እርሱ ልጅ ማለትም ቃል ነው:: እርሱ የእግዚአብሔር ፍፁም እውቀትና





ጥበብ ነው:: የእግዚአብሔር እውቀትና ጥበብ ደግሞ ከዘላለም ጀምሮ በእግዚአብሔር ውስጥ የሚኖር ነው፤ መለኮታዊ እውቀት ወይም ጥበብ ከእግዚአብሔር (ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ) የተወለደ ነው፤ እግዚአብሔር አብም አባት ነው፤ ይህም ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ነው::

<u>ዓለም ሳይፈጠር</u>:

ጌታችን ለአይሁድ፤ «አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» አላቸው:: (ዮሐ 8÷56) ይህ ማለት መለኮትነቱን በተመለከተ ሲናገር ከአብርሃም በፊት ነበርኩ ማለቱ ነው:: እንዲሁም የአብርሃም ልጅ የዳዊት ልጅ ቢባልም «እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ» (ራዕ 22÷16) አለ:: ከመለኮቱ አንፃር እርሱ የዳዊት ሥር ሲሆን ሰው ከመሆኑ አኳያ ደግሞ የዳዊት ዘር ነው::

ከመለኮትነቱ አንፃር ከአባቱ ጋር ባደረገው ንግግር በ(ዮሐ 17) እንደገለፀው ከዳዊት በፊት ነበር:: «አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ::» (ዮሐ 17÷5)

ዓለም ሳይፈጠር መኖሩ የተለመደ ነው፤ ምክንያቱም ዓለሙም በእርሱ ሆነ (ዮሐ 1÷10) ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም:: (ዮሐ 1÷3) ይላልና:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ እርሱ ሲናገር እግዚአብሔር አብ «ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ...በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» ብሏል:: (ዕብ 1÷2)

በእርግጥም ዓለማት ከተፈጠሩበት ከዘመናት በፊት (ዓለም ሳይፈጠር) እርሱ መኖር አለበት... እግዚአብሔር በትንቢተ ሚክያስ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ቤተልሔም ኤፍራታ እንደተናገረው ከዘላለም ጀምሮ ይኖራል «ከአንቺ



www.ethiopianorthodox.org

ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል::» (ሚክ 5÷2)

በሥጋ በተወለደ ጊዜ ከቤተልሔም ወጣ፣ ነገር ግን ዓለም ሳይፈጠር ከዘላለም ጀምሮ ከአብ ተወልዷል::

ነቢዩ ዳንኤል ስለእርሱ «ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው::» (ዳን 7÷14) አለ::

<u>ከብርሃን የተገኘ ብርሃን</u>:

እርሱ ብርሃን ነው የተባለው ከሥነ መለኮታዊው ግንዛቤ አንፃር እንጂ ከቁሳዊው ግንዛቤ አንፃር አይደለም::

እርሱ ስለራሱ ሲናገር፤ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም፤» (ዮሐ 8÷12) አለ:: እዚህ ላይ የተጠቀሰው ብርሃን ቁሳዊው ብርሃን አይደለም:: ስለ እግዚአብሔር «እርሱ ብርሃን ነው፤» (1ዮሐ 1÷5) ሲባል ስለ እግዚአብሔር አብም «የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም» (1ጢሞ 6÷15-16) ተብሏል::

አንዳንዶቹ ጌታችን «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» እንዴት ሊል ይችላል? በማለት ይደነቃሉ (ማቴ 5÷14) ምክንያቱም «እኔ የዓለም





ብርሃን ነኝ» ብሏልና (ዮሐ 8÷12) ታዲያ ልዩነቱ ምንድር ነው? ልዩነቱ የሚገለጸው በጸሐይና በጨረቃ ምሳሌ ነው:: በፍጥረት ታሪክ ውስጥ «እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን» (ዘፍ 1÷16) ተብሎ ተጽፏል:: ይህ ማለትም ጸሐይና ጨረቃ ማለት ነው:: ይሁንና ፀሐይ በራሷ ብርሃን ናት በሌላ በኩል ደግሞ ጨረቃ በራሷ ብርሃን የላትም ጨረቃ ብርሃን የምትሰጠው ፀሐይ በእርሷ ላይ በምታንፀባርቅባት ብርሃን አማካይነት ነው::

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወደ ዓለም በመምጣት ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ነው::» (ዮሐ 1÷9) እኛም ብርሃን የሆንነው ከርሱ ባገኘነው ብርሃን ነው::
በእርሱ ብርሃን ብርሃን አየን:: ስለ መጥምቁ ዮሐንስ «ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ:: ስለብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ብርሃን አልነበረም:: (ዮሐ1÷7-8) እንደተባለ እርሱ ባበራልን ብርሃን እኛም ብርሃን መስጠት ቻልን::

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባህርይ ሊደረስበት የማይችል ብርሃን ነው:: ነገር ግን ሥጋ በሆነ ጊዜ በእኛም መካከል በሆነ ጊዜ እርሱን ልንቀርበው ቻልን::

<u>ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ</u>:

«እውነተኛ አምላክ» ማለታችን እውነተኛ አምላክ ሳይሆኑ አማልክት ወይም ጌቶች እንደሚባሉት ሳይሆን በእውነት እርሱ የእግዚአብሔር ባህርይ አለው::



www.ethiopianorthodox.org

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን: እግዚአብሔር «እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ» (ዘጸ 7÷1) ያለው ሙሴ ይጠቀሳል:: «አምላክ አድርጌ» የሚለው ቃል ፈጣሪ፤ ዘላለማዊ ወይም ሁሉን የፈጠረ (የሚገዛ) ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ሙሴ ራሱ እግዚአብሔርን «እኔ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም አለ::» (ዘጻ 4÷10) ዳግመኛም «እነሆ እኔ ከንፈሬ ቈላፍ ነኝ እንዴትስ ፈርዖን ይሰማኛል? አለ::» (ዘጻ 6÷30) እግዚአብሔርም ሙሴን አለው:- «እኔ ለፈርኦን አምላክ አድርጌሃለሁ፤» (ዘጻ 7÷1) ማለትም እግዚአብሔር ለሙሴ በፈርዖን ላይ የበላይነትን ሰጥቶታል ማለት ነው::

በተመሳሳይም እግዚአብሔር ሙሴ ኮልታፋና ምላሱም ጸያፍ በመሆኑ ወንድሙ አሮንን አንደበት አድርጎ እንደሰጠው ነግሮታል:: «አንተም ትናገረዋለህ ቃሉንም በአፉ ታደርገዋለህ እኔ ከአፍህና ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፤...እርሱ ስለ አንተ ከሕዝቡ ጋር ይናገራል:: እርሱ አፍ ይሆንሃል አንተም በእግዚአብሔር ፈንታ ትሆንለታለህ::» (ዘጸ 4÷15፣16) በእግዚአብሔር ፋንታ ትሆንለታለህ ማለት የሚናገረውን ነገር እንደሚመክረው ለማስታወስ እንጂ እንደ ፈጣሪ እንደ እግዚአብሔር ትሆንለታለህ ማለት አይደለም፤ አሮንም በዕድሜ ከሙሴ የሚበልጥ እና ከሙሴ በፊት የተወለደ ነው::

«አማልክት» የሚለው ቃልም የሕዝቦችን አማልክት እና የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የሚጠሩትን በርካታ ሰዎች ለማመልከትም የሚያገለግል ነው:: በመዝሙር (82) ውስጥ «እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ በአማልክትም መካከል ይፈርዳል:: እስከመቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ?»





ተብሏል:: በእርግጥ እነዚያ ሐሰተኛ አማልክት እውነተኛ አማልክት አይደሉም:: በዚሁ ተመሳሳይ መዝሙር ውስጥ «እኔ ግን:- አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ:: ነገር ግን እንደሰው ትሞታላችሁ:: ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ አልሁ::» (መዝ 82÷6-7) ተብሎ ተጽፏል:: በእርግጥም የሞቱትም ሆኑ የወደቁት አማልክት ተብለው ቢጠሩም እውነተኛ አማልክት አይደሉም::

በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ «እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና፤ በአማልክትም ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና» (መዝ 95÷3) ተብሎ ተጽፏል:: «አማልክት» የሚለው ቃል በአሕዛብ ላይ ታላቅ አማልክት ተብለው የሚጠሩ እንጂ እውነተኛ አማልክት አይደሉም:: በተጨማሪም «እግዚአብሔር ታላቅ ምስጋናውም ብዙ ነውና በአማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነውና የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸውና» (መዝ 96÷4፣5) ተብሏል:: ነገር ግን ይህንን በተመለከተ አማልክት ተብለው ይጠራሉ::

ጌታችን ኢየሱስን በተመለከተ ግን የመለኮት ሁሉም ባህርያት ያሉት እውነተኛ አምላክ ነው::

እርሱ ዘላለማዊ፣ ፈጣሪ፣ ሁሉን የሚገዛ፣ በሁሉ የሚገኝ፣ የማይወሰን፣ ልብንና አእምሮን (ኩላሊትን) የሚመረምር የጌቶች ጌታ፣ ኃጢአትን ይቅር የሚል.... እና ሌሎች የእግዚአብሔር ባህርያት ሁሉ ያሉት ነው::

ለምሳሌ:- (ሮሜ 9÷5)፣ (ዮሐ 1÷1)፣ (1ጢሞ 3÷16)፣ (ሐዋ 20÷28)፣ እና (ራዕ 18÷11÷17)ን ተመልከት::

እርሱ እውነተኛ አምላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ እውነተኛ



www.ethiopianorthodox.org

አምላክ ነው:: እያንዳንዳቸው አብና ወልድ ሁሉም መለኮታዊ ባህርያት ያሏቸው ክብርና ኃይልም ለዘለዓለም የተሰጣቸው እውነተኛ አምላክ ናቸው::

<u>የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ:</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ አውግስጢኖስ እንደተነገረው ሁለት ጊዜ ተወልዷል:: ከአብ ያለ እናት ከዘላለም ጀምሮ ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ እንዲሁም ጊዜው ሲደርስ ከሴት(ከድንግል ማርያም) ያለ አባት ተወልዷል:: እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ የተወለደ እንጂ የተፈጠረ አይደለም፤ ከዘላለም ጀምሮ የተወለደ በመሆኑ «ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍፃሜ የለውም፤» (ዕብ 7÷3) ለዘመኑም ጥንት ስለሌለው የተፈጠረ አይደለም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ፍጥረት የተፈጠረበት ዘመን ወይም ጥንተ-ዘመን አለው::

ጸሎተ ሃይማኖት የአርዮስን የክህደት ትምህርት የሚፃረር ትምህርት ይደመጥበታል:: ሐሳቦች ከአእምሮ ጨረሮችም ከጸሐይ እንደሚወለዱ ኢየሱስ ክርስቶስም (ወልድም) ከአብ የተወለደ ነው:: ስለዚህ እርሱ:

<u>በባህርዩ ከአብ ጋር የሚተካከል ነው:</u>

ይህ ቃል «ከእኔ አብ ይበልጣል» የሚለውን የጌታችንን ቃል በተሳሳተ መንገድ ለተረዱት ለአርዮሳውያን አስተሳሰብ መልስ የሰጠ ነው:: በመሠረቱ ከሕልውና አንጻር አብ ከወልድ አይበልጥም ምክንያቱም ወልድ ከአብ ጋር የሚተካከል (አንድ የሆነ) ባህርይ፣ ሕልውና እና መለኮትነት አለው:: በሁሉም ነገር እኩል ናቸው::





«ከእኔ አብ ይበልጣል» የሚለውን ሐረግ በተመለከተም ይህን ቃል የተናገረው ሥጋን በመልበስ ራሱን ባዶ ስለማድረጉ የተናገረው ነው፤ «በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ» ተብሎ ተጽፏልና (ፊል 2÷6-8)::

መለኮትነቱ ሳይለወጥ (ሳይለየው) የባሪያን መልክ መያዙ «ከእኔ አብ ይበልጣል» ሲል የተናገረውን ሁኔታ ያስረዳል::

ወልድ በሰው ምሳሌ ሆኖ በተቀበላቸው መከራዎች፣ በመስቀሉ እና በነቀፌታዎች እግዚአብሔር አብ ይበልጣል:: ከሰብአዊ ባህርዩ ጋር የተዋሃደው አምላክነቱ ግን በሥጋ ትህትና ምክንያት ስላልተጠቃ አልተለወጠም::

በሥጋ ሆኖ እንዲናገርና እንዲሠራ ያስቻለው ከአብ ጋር እኩል የሆነውና በውስጡ ያለው መለኮትነቱ ነው::

«እኔና አብ አንድ ነን፤» (ዮሐ 10÷30)፤ «እኔን ያየ አብን አይቷል» (ዮሐ 14÷9)፤ «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ አለ» (ዮሐ 14÷10) «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያክብሩት» (ዮሐ 5÷23) ሲል ለሽባውም ሰው «ኀጢአትህ ተሠረየችልህ» (ማር 2÷5-10) አለው፤ እግሮቹን በእንባዋ ላጠበቻቸው እንዲሁ አላት:: እንዲሁም በለበሰው ሥጋ በባህር ላይ ተራመደ(ማቴ 14:25)፣ ነፋሱንና ማዕበሉን ገሠጸው፣ ጸጥም አደረገው(ማር4:39):: ሥጋ ለብሶ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣን በተአምር አበርክቷል(ማቴ 14:17) በቃና ገሊላ ሠርግ ላይ ተገኝቶም ውኃውን ወደ



www.ethiopianorthodox.org

ወይን ቀይሯል። (ዮሐ፡2) እንዲሁም እውር ሆኖ ለተወለደው ሰውም ብርሃን በመስጠት ተአምር ሠርቷል(ዮሐ 9) ከዚህ ከተጨማሪም አምላክነቱን የሚገልፁ በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። በትንሣኤው ጊዜ በድንጋይ ከተዘጋ መቃብር መውጣቱ እና በሮቹ በተዘጉበት ቤት ጣሪያ መግባቱ (ዮሐ 20፡19) እንዲሁም ወደሰማይ ማረጉ ሁሉም የአምላክነቱ መገለጫ ምሳሌዎች ናቸው።

<u>ሁሉ በእርሱ ሆነ፡</u>

እዚህ ላይ ጸሎተ ሃይማኖት እግዚአብሔር ወልድ ሁሉን የፈጠረ ፈጣሪ መሆኑን ይናገራል፣ በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል "ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" (ዮሐ1፡3) ተብሎ እንደተነገረው ለቈላስይስ ሰዎች በተላከው መልእክትም "ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል" (ቈላ 1፡16) ተብሏል።

እዚህ ላይ ቀጣዩን ጥያቄ እንጠይቃለን። ዓለምን ማን ፈጠረ? እግዚአብሔር አብ ወይስ እግዚአብሔር ወልድ? መልሱ ሁሉንም ነገር በልጁ በኩል ፈጠረ የሚለው ነው።

"የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና" (ቈላ 1፡16) እርሱ የእግዚአብሔር ፍፁም ጥበብ ነው፤ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በጥበቡ እና በቃሉ ፈጥሯልና። ስለዚህም "የእግዚብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው" (1ቆሮ 1፡24)።





<u>ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ፡</u>

እግዚአብሔር ወልድ ሰው ከሆነበት አላማው ባሻገር፡-

- ለሰው "በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል" የተፈጠረበትን ትክክለኛውን አርአያ መልሶለታል። ነገር ግን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በምድር ላይ በሚኖረው ሕይወት የቀድሞውን አርአያ እስኪመልስለት ድረስ ሰው ይህንን መለኮታዊ አምሳል አጥቶ ኖሯል።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን በአንፀባራቂ ትምህርት ለመሙላት እና መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለሚዘጉ እነርሱም የማይገቡ ሆነው የሚገቡትንም እንዳይገቡ በሚከለክሉ ግብዞች ጻፎች ፈሪሳውያን ምክንያት የተሠራጩት ስህተት የሆኑ ትምህርቶችን ለማስተካከል መጣ (ማቴ 23፡13)። በተራራው ስብከቱ ላይ "እንደተባለ ሰምታችኋል..... እኔ ግን እላችኋለሁ" (ማቴ ፡5) የሚለውን ቃል ደጋግሞ የተናገረውም ለዚህ ነው።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች እግዚአብሔር እነርሱን የሚወዳቸው ሰማያዊ አባት እንደሆነ ሊናገር መጣ።

- ለድሆችና ለነዳያን (ለተቸገሩት) አገልግሎቱን ይፈጽም ዘንድ መጣ፤ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ ስለእርሱ ሲናገር «ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ ለተማረኩትም ነፃነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል።» (ኢሳ 61፥1) ብሎአልና። ስለዚህ በነቢዩ በሕዝቅኤል እንደተጻፈው የመልካም እረኝነትን



www.ethiopianorthodox.org

> ምሳሌ ለዓለም አቀረበ:: «እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸዋለሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር:: የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ::» (ሕዝ 34÷15)

ይሁንና የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነበት መሠረታዊው አገልግሎት ሰዎችን ማዳን ነበር::

እርሱ የሠራው ሰዎችን የማዳንን ሥራ ብቻ ነበር:: ይህም በአገልግሎቱ በቂ ሥራ ነበር:: ነገር ግን በተግባር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች እርሱን እንዲያውቁት የተወሰነ ነገር መሥራት ስለነበረበት የማዳንን ሥራ ከመሥራቱ በፊት የተለያዩ አገልግሎቶችን ፈጽሟል:: ስለዚህም የመምህርነትን፣ ለጠፉት በጎች እረኛ ለሰዎች ምሳሌ የመሆንን እንዲሁም በፍቅር የተሞላ ልብ የመሆንን አገልግሎት ፈጽሟል::

ስለእኛ ከሰማይ ወረደ፤
ይህ ማለት ሰማይ የእርሱ ቤት ነው ማለት ነው::

ስለዚህም እርሱ ራሱ «ከአብ ወጥቼ ወደዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ::» (ዮሐ 16÷28) ሲል እንዲሁም «እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል?» (ዮሐ 6÷62) አለ:: ስለዚህ አስቀድሞ በሰማይ ነበረ፤ ከሰማይም ወደምድር ወረደ፤ ታዲያ ለኒቆዲሞስም ይህን አስመልክቶ «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደሰማይ የወጣ ምንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው::» (ዮሐ 3÷13) አለው::





አስቀድሞ በሰማይ መኖር የመለኮትነቱ ማረጋገጫ ነው::

ቅዱሳኑ እንደተናገሩት አምላክ የሆነ ሰው ሳይሆን ሰው የሆነ አምላክ ነው፤ ራሱን ባዶ አድርጎ የባሪያን መልክ የወሰደና በሰዎች አምሳል የመጣ... ለሁላችንም ድኅነት::

«ከሰማይ ወረደ» የሚለው ቃል ሰማይን ትቶ መጣ ማለት አይደለም:: «ከሰማይ ወደ ምድር ቢወርድም በሰማይም አለ ምክንያቱም እርሱ በሁሉ ቦታ ያለ እና በእርሱ ዘንድ ባዶ ቦታ ፈጽሞ (እርሱ የሌለበት ቦታ) የለም:: ለኒቆዲሞስ በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው::» (ዮሐ 3÷13) ያለው ለዚህ ነው:: ይህ ማለት በሰማይ እያለ ከሰማይ ወደምድር ወረደ ማለት ነው::
«ከሰማይ ወረደ» ማለት በአንድ በኩል ራሱን ባዶ አደረገ (ፊል 2÷7) ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ራሱን ለእኛ ገለጠ ማለት ነው::

ከሰማይ ወረደ ማለት የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ በይበልጥም፤ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ (ፊል 2÷7፣8) ማለት ነው::

«ከሰማይ ወረደ» የሚለው ቃል ሐዋርያው እንደተናገረው በሥጋ ለእኛ ተገለጠ ማለት ነው፤ «እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤» (1 ጢሞ 316) እንዳለ:: ስለዚህ የማይታየው ታየ ማለት ነው::

«ሥጋ ሆነ» ማለት ሥጋን ከሰው ወሰደ ማለት ነው:: ማለትም:- መለኮታዊው ባህርዩ ከሥጋ ጋር ተዋሐደ ማለት ነው:: ነገር ግን ሥጋን



www.ethiopianorthodox.org

እንዴት ሊያገኘው ቻለ? ከማንስ አገኘው?

<u>በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ:</u>
ድንግል ማርያም ወንድ ስለማታውቅ ልጅ ልትወልድ አትችልም (ሉቃ 1÷34) ስለዚህም መልአኩ ጉዳዩን ግልፅ በማድረግ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል» (ሉቃ 1÷35) አላት::

መንፈስ ቅዱስ በማህፀኗ አደረ፤
ይህ ብቸኛና የተለየ ሁኔታ ነው ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ማህጸን አያድርም ነገር ግን በድንግል ማርያም ማህጸን ስለሁለት ምክንያቶች በእርስዋ ላይ መጣ፤ የመጀመሪያው ወንድ ሳታውቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በማህጸኗ እንዲያድር ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ማህጸኗን ለመቀደስ ነው::

ከእርስዋ የሚወለደው ቅዱስ ነው (ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር እኛን የሚመስል ነው::) ስለዚህ እርሱ የሞተው ስለራሱ ኃጢአት ሳይሆን ስለእኛ ኃጢአት ነው:: ምክንያቱም እርሱ ኃጢአት የለበትም::

«ሥጋ ሆነ» የሚለው ቃል የሰውን ሥጋ ወሰደ ማለት ብቻ ሳይሆን የሰውንም ተፈጥሮ (ባህርይ) ጭምር የሆኑትን ሥጋና መንፈስን ወሰደ ማለት ነው:: ስለዚህ ጸሎተ ሃይማኖት ሥጋ ሆነ የሚለው ቃል ላይ አላቆመም ይልቁንም ሰው ሆነ የሚለውንም ቃል ጨምሮበታል::





<u>ሰው ሆነ:</u>
ሐዋርያው እንደተናገረው ሰብአዊ ባህርይን በመውሰድ ፍፁም ሰው ሆኗል፤ አንድ «እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ:: እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (1 ጢሞ 2÷5) ሰው የሆነበት ምክንያት ደግሞ በሰው ላይ ተፈርዶበት ስለነበር ከሰው ባህርይ ጋር የተወለደው ሰው የሆነው እርሱ፣ ፍርድ ከሰዎች ላይ እንዲወገድ የሚሞተው እርሱ ከሰው ባህርይ ጋር ሰው መሆን ነበረበት:: ፍጹም ሰው ባይሆን ኖሮ በሁሉም ነገር እኛን አይመስልም ነበር፤ ሞት የተፈረደበት ባህሪያችንንም አይወስድም ነበር::

በጸሎተ ሃይማኖት እና በቅዱስ ቁርባን (በሥርዓተ ቅዳሴ) ውስጥ «ሥጋ ለበሰ፤ ሰውም ሆነ» ተብሎ የተገለጸው የክርስቶስን ፍጹም ሰብአዊ ባህርይ በእርሱም ራሱን ለኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ በሰዎች ፈንታ መስጠቱን የሚመሠክር ቃል ነው:: ስለዚህም ሐዋርያው «በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ (1 ጢሞ 2÷5-6) አለ::

ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰው ልጅ» በሚለው መጠሪያ ተደጋግሞ የሚጠራው ለሰዎች ኃጢአት ሲል የሞተው ሞት ሰውን በአጠቃላይ የሚወክል በመሆኑ ነው:: አስቀድሞ ከተቀደሰው የጽንሰት ቅጽበት ጀምሮ በድንግል ማህፀን ውስጥ ከመለኮት ጋር የተዋሀደ ቅዱስ ሰው ሆነ፤ የድንግል ማህፀንም ወደ እርሷ በወረደው በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ:: ይሁንና ቅድስት ድንግል ማርያም እርሱን በመጸነሷ እንደሌሎች ሰዎች ድኅነትን ስለፈለገች



www.ethiopianorthodox.org

በምስጋና መዝሙር «መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤» (ሉቃ 1÷47) አለች::

<u>ስለእኛ ተሰቀለ</u>:

በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ::

ስለእኛ ተሰቀለ ማለት ለእኛ ሲል ወይም በእኛ ፈንታ ማለት ነው:: ኃጢአት ስለሠራን ሞት የተገባን ሆንን «የኃጢአት ደሞወዝ ሞት ነውና፤» (ሮሜ 6÷23) እንዲሁም «...ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» (ሮሜ 5÷12) ተብሎአልና::

ስለዚህ ኃጢአት የሌለበት ክርስቶስ በሞት ፍርድ ሥር ባሉት በኃጢአተኞች ፈንታ ሊሞት መጣ::

ይህን በመመስከር በኢየሱስ ክርስቶስ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ስለኢየሱስ ክርስቶስ በመከራከር በሌላኛው ጎን የተሰቀለውን ተጠራጣሪ (ተሳዳቢ) ወንበዴ «ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሰጸው::» (ሉቃ 23÷41)

በመጨረሻም ይሰቀል ብሎ የፈረደበት ጲላጦስ እንኳን ክርስቶስን ወደ እርሱ ለላኩት ለሊቀ ካህናቱና ለአይሁድ ገዢዎች «ለሞት የሚያደርስ በደል አላገኘሁበትም» (ሉቃ 23:22÷14) አላቸው:: ቀጥሎም እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹህ ነኝ::» (ማቴ 27÷24) አላቸው:: ታዲያ ምንም በደል የሌለበት ሞት ለሚገባን ለእኛ ሲል ተሰቀለ::

እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ





መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ:: (ኢሳ 53÷6)

እኛን በሞቱ ለማዳን ሞተ ማዳን ማለት ደግሞ ሞት የማይገባው ስለበደለኞች ሞተ ማለት ነው:: ኃጢአተኛ ስለኃጢአቱ ይሞታል ኃጢአት የሌለበት ስለሌሎቹ ኃጢአት ከሞት አዋጅ ለማዳን ይሞታል:: ምንም ጻድቅ አንድም እንኳን ጻድቅ አልነበረም፤ «ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም::» (መዝ 14÷3)

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሌሎቹ የሞተ ቅዱስ ነው፤

ቅዱስ ገብርኤል ክርስቶስን እንደምትወልድ ለቅድስት ድንግል ማርያም ሲያበስር «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::» (ሉቃ 1÷35) አላት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም አይሁድ ክርስቶስን ስለመስቀላቸው ሲወቅሳቸው «እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ» (ሐዋ 3÷14) አላቸው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ክርስቶስ ሲናገር «ቅዱስና ያለተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል» (ዕብ 7÷26) አለ:: እርሱ ቅዱስ ቢሆንም ኃጢአታችን ተሸከመ::

በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኃጢአታችንን ተሸካሚ ሆኖ እንጂ ኃጢአተኛ ሆኖ አልነበረም::

እርሱ የሌሎቹን ኃጢአት፤ የዓለምን ኃጢአት፤ ያለፈውን ኃጢአት፤ የዛሬውን ኃጢአትና የሚመጣውን ኃጢአት ተሸክሞአል:: ሐዋርያው ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ «ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰረያ ነው፤ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ እንጂ» (1 ዮሐ 2÷1፣2) ብሏል:: መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስም፤ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ (ዮሐ 1÷29) ሲል ተናግሮለታል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች እና የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች የእርሱ ምሳሌ ብቻ እንደሆኑ አስታውሶናል::

በብሉይ ኪዳን ኃጢአተኛው ለኃጢአቱ ማስተስረያ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር:: መሥዋዕቱም ኃጢአተኛው እጁን በእንሰሳው ላይ ጭኖ ኃጢአቱን የሚናዘዝበት ንጹህ እንስሳ ነው:: እጁን በመሥዋዕቱ ላይ መጫን ማለት ኃጢአተኛው መሥዋዕቱ በእርሡ ቦታ እንዲሆን ተስማምቷል ማለት ነው:: በዚህም ኃጢአቱ ወደ መሥዋዕቱ ይተላለፋል ማለት ሲሆን እንስሳውም በእርሱ ፈንታ ይሞታል ማለት ነው:: እነዚያ የሚሠውት ንጹህ እንስሳት ኃጢአተኞች ሳይሆኑ ኃጢአትን የሚሸከሙ፤ እንስሳቱ ኃጢአተኞችን ወክለው ለማስተሰረያ እንደሚሆኑ የሚያምኑ ኃጢአተኞችን ኃጢአት የሚሸከሙ ናቸው::

የኃጢአቱ መሥዋዕት ቅዱስ ቅዱሳን ተብሎ ተገልጿል (ዘሌ 6÷25)
ቅዱስ ቅዱሳን ተብሎ የተገለጸው ይህ የኃጢአት መሥዋእት በ(ዘሌ 6÷29) ላይም ተደግሟል ስለዚህ የሚቃጠለው መሥዋዕት በሚታረድበት ቦታ ይታረዳል በመጨረሻም የሚቃጠለው «በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ» (ዘሌ 1÷9) ተብሎ ተገልጿል::





ይህ መግለጫ «የእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ» እና «ለእግዚአብሔር የሚሆን የእሳት ቁርባን» (ዘሌ 2÷2፣3፣9፣10) ለሆነው ለእህል መሥዋዕትም ተሰጥቷል:: በተመሳሳይ የበደል መሥዋዕትም «ቅዱስ ቅዱሳን» ተብሎ ተጠርቷል (ዘሌ 7÷2)

ስለዚህ `ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት በተሸከመ ጊዜ የኃጢአት የበደል እና ቅዱስ ቅዱሳን የተባለ መሥዋዕት ነበር፤ እንዲሁም «በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ» ነበር::

ነገር ግን በመስቀል ላይ መሞትን ለምን መረጠ?

<u>አንደኛ</u>:- ይህን አይነት ሞት ሁሉንም የሰውነት ደም ስለሚያፈስስ እና ሰውነት ላይ የሚመቱት ምስማሮች ከሚፈጥሩት ህመም በተጨማሪ ነርቮችን ስለሚነካ እጅግ አሰቃቂ ነው::

<u>ሁለተኛ</u>:- የመስቀል ላይ ህመም ለረዥምም ሰዓት የሚዘልቅ ነው:: ለምሳሌ:- ራስን መቅጨት ማቃጠል ወይም በገመድ ታንቆ (ተሰቅሎ) መሞት ጥቂት ቅጽበትን ብቻ የሚወስድ ነው ሌሎችም ሞቶች ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ሊወስዱ ይችላሉ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ መሞት ግን የስቅለትን ዝግጅት ሳያጠቃልል ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ለሦስት ሰዓታት ያህል ይቆያል::

<u>ሦስተኛ:-</u> መስቀል የንቀት ምልክት እና በከተማ ውስጥ እና ከከተማ ውጭ ለሁሉም ህዝብ በሚታይ በከፍተኛ ቦታ ላይ የሚፈጸም በመሆኑ ቅጣትን መግለጫ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

<u>አራተኛ፡-</u> በብሉይ ኪዳን ዘመን በሙሴ ህግ (ዘዳግ 21÷22፤23) እንደ እርግማን ይቆጠር ነበር:: በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና (ገላ 3÷13) ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፋንታ እርግማንን በመስቀል ላይ ተሸክሞ እኛን ከህግ እርግማን ነፃ አወጣን::

ስለዚህ በመስቀል ላይ መሞት ውርደት ነበር ስለእርሱም «በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ::» (ፊል 2÷8) ተብሏል::

በመስቀሉ ሞታችንን፤ ሃፍረታችንን እና እርግማናችንን ተክቶልናል:: ይህ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም መጾም የማይገባው እርሱ ስለ እኛ ጾመልን፤ ጥምቀት ወይም ንስሐ የማይገባው እርሱ ስለ እኛ ፋንታ ወደንስሐ ጥምቀት ወረደልን::

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ተሰቅሏል ይህም በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ «በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ» ተብሎ ተገልጿል::

ይህም ጸሎተ ሃይማኖት የጌታችን ስቅለት መቼ እንደተከናወነ ትክክለኛውን ጊዜ እና በየትኛው የሮማ ዘመነ መንግሥት እንደተፈፀመ ለማስገንዘብ ያተተው ታሪካዊ ሁነት ነው::

<u>መከራን ተቀበለ</u>:

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መቀበሉን ማረጋገጥ ወሳኝነት አለው::

ነገር ግን ይህን አስረግጦ መናገር ለምን ጠቃሚ ሆነ? አንዳንዶቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የተዋሃዱት መለኮት እና ሰብአዊነት የኢየሱስ ክርስቶስን





ሰብአዊ ባህርይ ከሥቃይ ጠብቆታል ብለው ስለሚያስቡ ነው!

ይህ ሃሳባቸው እውነት ቢሆን ኖሮ ስቅለት ሥርዓት ብቻ ይሆን ነበር እንጂ ክርስቶስ ቃል በገባው መሠረት የሞትን ዋጋ አይከፍልልንም ነበር::

የመስቀሉ መከራዎች ነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ በትንቢቱ እንደተናገረው አስቀድሞ የተቀመጠ እውነት ነው፤ «የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ....በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው:: እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ...እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ ነፍሱን ስለኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኂላ ዘሩን ያያል::» (ኢሳ 53÷3-10)

በመስቀል ላይ ከተቀበለው ታላቅ ሥቃይ የተነሣ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?» (ማር 15÷34) ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ከውስጡም ከፈሰሰው ደም እና ፈሳሽ የተነሣ «ተጠማሁ» (ዮሐ 19÷28) አለ::

በእርግጥም ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አስጨናቂ ሥቃዮችን ተቀብሏል አባቱም (እግዚአብሔር አብም) ሊያሰቃየው እና በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ:: ነገር ግን «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?» የሚለው ዓረፍተ ነገር መለኮትነቱ ተለይቶታል ማለት ሳይሆን እውነታው እግዚአብሔር እንዲሰቃይ ፈቅዷልና ሥቃዩን አላስወገደለትም ማለት ነው:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበላቸውን መከራዎች ለማስታወስ በየዓመቱ ታከብራለች ከበዓለ ሃምሳ ወቅት በስተቀር ያሉትን ሁሉንም ረቡዕና ዓርብ በጾም ታስባቸዋለች:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰብአዊ አካሉ



www.ethiopianorthodox.org

ዕረፍት ለመሥጠት መለኮትነቱን (አምላክነቱን) ፈጽሞ አልተጠቀመም::

ይህንን ያደረገው ደግሞ በስቅለቱ ወቅት ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ በሥጋ በተመላለሰበት ወቅትም ሁሉ ጭምር ነው:: ከሔድሮስ ሰይፍ ለማምለጥ ወደግብፅ በሸሸበት ወቅት መለኮታዊ ኃይሉን ተጠቅሞ ሔሮድስን በሞት ሊያጠፋው ይችል ነበር:: ነገር ግን ይህን አላደረገም የመለኮት ኃይሉንም አልተጠቀመም::

በተራራ ላይ በጾመበት ጊዜም መለኮቱ ሥጋውን ከረሃብ ይጠብቀው ዘንድ ይችል ነበር:: ነገር ግን ይህን አላደረገም «አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጦመ በኋላ ተራበ» (ማቴ 4÷2) ይላልና:: ስለዚህ ሥጋው ተርቧል፤ ለሥጋው ምቾትን ይሠጠው ዘንድም መለኮታዊ ሃይሉን አልተጠቀመም ሰይጣን እንደፈተነውም ድንጋዩን ወደ ኅብስት (ዳቦ) ሊቀይር አልተስማማም!!

በምድር ላይ በሥጋ በተመላለሰባቸው ጊዜያት ሁሉ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ ደክሞአል፣ ተሰቃይቷልም፤ ታዲያ እነዚህን ሁሉ ለመከላከል ግን መለኮቱን ፈፅሞ አልተጠቀመም:: በተጨማሪም መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ በወጣ ጊዜ (ዮሐ 19÷17) ከብዙ ድካም የተነሣ እየወደቀ ተንገላቷል ቀሬናዊው ስምዖንም መስቀሉን ተሸክሞለታል (ማር 15÷21) የቀሬናው ሰው ሳያስፈልግ መስቀሉን በመለኮቱ ሃይል መሸከም ይችል ነበር:: ነገር ግን ይህን አላደረገም የዘበቱበትንና የተፉበትንም ለማስቆም መለኮቱን አልተጠቀመም:: (ማቴ 27÷29-31)

ከስቅለቱ አስቀድሞ ስለእነዚህ መከራዎች ትንቢት ተናግሮአል:: ለደቀመዛሙርቱ «ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን





ይነሣ ዘንድ እንዲገባው» (ማቴ 16÷21) ገልጦላቸዋል:: «የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባቸው ያስተምራቸው ጀመር::» (ማር 8÷31) «ስለ ሰው ልጅም እንዴት ተብሎ ተጽፏል? ብዙ መከራ እንዲቀበል እንዲናቅም» (ማር 9÷21) (ሉቃ 9÷22) ዳግመኛም «...የሰው ልጅ በቀኑ እንዲሁ ይሆናል:: አስቀድሞ ግን ብዙ መከራ እንዲቀበል ከዚህም ትውልድ እንዲጣል ይገባዋል::» (ሉቃ 17÷25)::

ከትንሣኤውም በኋላ ነቢያት አስቀድመው ስለ እርሱ መከራዎች ትንቢት መናገራቸውን ተናገረ::

ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ የነበሩትን ሁለት ደቀመዛሙርት «እናንተ የማታስተውሉ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን?» (ሉቃ 24÷25-26) አላቸው:: ለደቀመዛሙርቱም «ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል ተብሎ እንዲሁ ተጽፏል» (ሉቃ 24÷46) አላቸው::

<u>ለምሳሌ</u>:- የፋሲካው በግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር፤ «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» (1 ቆሮ 5÷7) እንደተባለ:: የመከራ ምሳሌ የሆነው የፋሲካው ጠቦትም በእሳት ይጠበስ ነበር (ዘጸ 12÷8)

በተጨማሪም የመለኮታዊውን ፍትህ በማሟላት በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ (ዘሌ 1÷9) በመሆን የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው የሚቃጠለው መሥዋዕትም በመሠዊያው ላይ ባለው እንጨት ላይ ሌሊቱን ሁሉ እስኪጸባ ድረስ የሚሆን እሳቱም «በመሠዊያው ላይ ዘወትር



www.ethiopianorthodox.org

የሚነድድ...የማይጠፋ» (ዘሌ 9÷12) መሆን አለበት:: እነዚህ ሁሉ እሳቶች ወደ አመድ እስኪለወጥ ድረስ በሚቃጠለው መሥዋዕት ለሚሟላው መለኮታዊ ፍትህ ምሳሌ ነበሩ::

<u>ተቀበረ</u>:

የኢየሱስ ሥጋ በአርማትያሱ ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከተከፈነ በኋላ በመቃብር ውስጥ ተቀብሮ ነበር፤ «የኢየሱስንም ሥጋ ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት:: በተሰቀለበትም ሥፍራ አትክልት ነበረ:: በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ:: ስለዚህ...ኢየሱስን በዚያ አኖሩት::» (ዮሐ 19÷40-42)፤ «ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ፤» (ሉቃ 23÷55)

ኢየሱስ የተቀበረበት መቃብር ከዓለት የተወቀረ መቃብር ነበር፤ ዮሴፍም የኢየሱስን ሥጋ በዚያ ሲያኖረው በመቃብሩ ደጃፍ ድንጋይ አንከባለለ:: (ማር 15÷46) «መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር::» (ማር 15÷47)

ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ የፈሩት የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ተሰብስበው እንዲጠበቅ እዘዝ ስላሉት መቃብሩ ይጠበቅና በድንጋዩም ላይ ታትሞበት ነበር:: (ማቴ 27÷62-66)

በአርማትያሱ ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ተከፍኖ





በአዲስ መቃብር የተቀበረውና በመቃብሩ ደጃፍ ድንጋይ ተንከባሎበት ብዙ ሴቶችም ይህንን ተመልክተው የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ድንጋዩን አትመው የመቃብሩን ጠባቂዎች በማስቀመጥ የተጠናቀቀው ይህ ሁነት የትንሣኤው ማረጋገጫ ነው ምክንያቱም ጠባቂዎች፣ ድንጋዩ እና ማህተሙ ባሉበት ደቀመዛሙርቱ እንዴት ሊሠርቁት ይችላሉ! ከዚህ በተጨማሪም የሰንበት ዋዜማ ነበር (ማር 15÷42) ህዝቡም እንደትእዛዙ ያረፈበት ዕለት ነበር፤ (ሉቃ 23÷56) ይሁንና፣ ይህ ሁሉ ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሣ፣ ባዶው መቃብርም ለትንሣኤው ማረጋገጫ ሆነ::

<u>ከሙታን ተለይቶ ተነሣ</u>:

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተፃፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተለይቶ ተነሣ::

ስለሚከተሉት ምክንያቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከሌሎች ሰዎች ትንሣኤ የተለየ ነው::

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣው በራሱ እንጂ በሌላ በማንም አይደለም::

በብሉይ ኪዳን ወደ ሕይወት የተመለሱ ሦስት ሰዎች ነበሩ:: በነቢዩ ኤልያስ ከሞት የተነሣው በሲዶና አጠገብ ያለችው የሰራፕታዋ ባልቴት ልጅ (1 ነገ 17÷22) በነቢዩ ኤልሳዕ ከሞት የተነሣው የሱነማይቱ ሴት ልጅ (2 ነገ 4÷25) እና ሦስተኛው ደግሞ ሬሳው በኤልሳዕ መቃብር ተጥሎ የኤልሳዕን አጥንት በነካ ጊዜ ድኖ በእግሩ የቆመው ሰው (2 ነገ 13÷21) ናቸው::

ሌሌች ሦስት ሰዎችም በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥተዋል:: የናይኗ



www.ethiopianorthodox.org

መበለት ልጅ (ሉቃ 7÷15) የምኩራብ አለቃው ሴት ልጅ (ሉቃ 8÷55) እና አልዓዛር (ዮሐ 11÷43-44)

ቅዱስ ጳውሎስም አውጤኪስ የሚሉትን አንድ ጎበዝ ከሞት አስነስቷል (ሐዋ 20÷10) ቅዱስ ጴጥሮስም ጣቢታን አስነሥቷል:: (ሐዋ 9÷40) ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ በሌሎች የተነሡ ናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በመለኮቱ ሃይል ከሞት የተነሣ አንዱና ብቸኛው ነው:: እርሱ ራሱ ተነሣ፤ ሌሎችን ግን ሌሎች አስነሷቸው::

2. በክቡር ሥጋ የተነሣው እርሱ ብቻ ነው::
በትንሣኤ ሙታን ስለምንለብሰው ሥጋችን ሲናገር፤ «መድኃኒታችን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን:: ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል::» (ፊል 3÷20፣21) አለ::

በትንሣኤ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ሥጋ በትልቅ ድንጋይ ከተዘጋ መቃብር ውስጥ መውጣት ችሏል:: ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው የነበሩበት ቤት ደጆቹ ተዘግተው ሳለ በቤቱ የላይኛው ክፍል መግባት ችሏል:: (ሐ 20÷19)

በዚህ ክቡር ሥጋ ወደሰማይ አረገ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው:: (ሐዋ 1÷9፣10)

ከትንሣኤው በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በላ:: እነርሱ መንፈስም ያዩ ስለመሰላቸው መነሣቱን ሊያረጋግጥላቸው ቁስሎቹን አሳያቸው:: (ሉቃ 24÷37-43)





3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣው እና ዳግመኛም የማይሞተው አንዱና ብቸኛው ነው::
በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዋርያት አስቀድመው ተነሥተው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ትንሣኤ ሙታንን ለመጠበቅ ዳግመኛ ሞተዋል:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶ ሕያው ሆኖ ይኖራል፤ ሕያው ነው:: ስለዚህ ሰዎች ሕያው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቢምሉ ወይም ወደ እርሱ ቢጸልዩ እንግዳ ነገር አይደለም::

ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን «ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል::» (1ቆሮ 15÷20) ብሎ ጠርቶታል::

እርሱ ከሙታን መካከል የተነሣውና ዳግመኛ የማይሞተው ፊተኛው ነው:: እርሱ ራሱ በራዕየ ዮሐንስ ለቅዱስ ዮሐንስ «ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ:: አሜን::» (ራዕ 1÷17-18) ያለው ለዚህ ነው::

የክርስቶስ ትንሣኤ ሐዋርያት የሰበኩት አይሁድም እጅግ የተሸበሩበት እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ «ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር:: በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው::» (ሐዋ 4÷33) ይላል:: ይህ የአይሁድ አለቆችን አስጨንቋቸዋል ምክንያቱም የክርቶስን ትንሣኤ ማወጅ መለኮትነቱን እና ቅድስናውን የሚያረጋግጥ በመሆኑ እንዲሁም አይሁድ ጨካኞች ሆነው እርሱን በመስቀላቸው ደሙ በእነርሱ ላይ በመሆኑ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ይህም አይሁድ ሐዋርያትን ጠርተው «በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆም ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል፤ የዚያንም ሰው ደም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስባላችሁ» (ሐዋ 5÷27፣28) እንዲሉ አደረጋቸው:: ሐዋርያት ግን አይሁድን «እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት::» (ሐዋ 3÷14፣15) ብለው ገሠጿቸው::

4. የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የኃይሉ እና የድሉ ማረጋገጫ እንዲሁም እኛን ከእርሱ ጋር እንደሚያስነሣ የታወጀበት አዋጅ ነው::

እርሱ በትንሣኤው ሞትን ድል የነሣ እና በኃይሉ ሞትን የረገጠ ነው:: ለትንሣኤያችን ቃል ኪዳን ሰጥቶናል «ሞት በሰው በኩል መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና::» ክርስቶስ እንደበኩራት ነው፤ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው:: (1 ቆሮ 15÷21፣23)

ይህ የትንሣኤ ሙታን ተስፋ በክርስቶስ ትንሣኤ የተገኘ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት:: ደግሞም ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል::...በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን:: አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል::» (1 ቆሮ 15÷13-20)





ክርስቶስ ያልተነሣ ቢሆን ኖሮ እንደማንኛውም ተራ ሰው በሆነ ጠላቶቹም ድል ባደረጉት ሞትም በእርሱ ላይ ድልን በተቀዳጀ ነበር!!

እርሱ ግን ተነሥቶአል ምክንያቱም «በእርሱ ሕይወት ነበረች» (ዮሐ 1÷4) እርሱም «የሕይወት ራስ» (ሐዋ 3÷15) እንዲሁም አልዓዛርን ከማስነሣቱ በፊት ለአልዓዛር እህት ለማርታ እንደነገራት «ትንሣኤና ሕይወት» (ዮሐ 11÷25) ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከስቅለቱ አስቀድሞ ለደቀመዛሙርቱ የተነገራቸው ጉዳይ ነበር::

ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ነግሯቸዋል:: (ማቴ 16÷21)፣ (ማር 8÷31) እና (ሉቃ 9÷22)::

ከትንሣኤው በኋላ ተገልጾላቸው ምን እንደሚፈጠር በነቢያት መገለጹን ነገራቸው:: እንዲህም አላቸው:- «ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል::» (ሉቃ 24÷46):: ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ወደ መቃብሩ ለመጡት ሴቶችም መላእክት ቀርበው እንዲህ አሉአቸው:- «ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም:: የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደተናገረ አስቡ::» (ሉቃ 24÷5-7)

የጌታችን በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል መነሣት በትንቢተ ዮናስ



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ውስጥ በተመሳሳይ ተቀምጦ ነበር::

ብዙ ምልክቶችን ከፈጸመ በኂላ አይሁድ ምልክት እንዲያሳያቸው በጠየቁት ጊዜ፣ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም:: ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል::» (ማቴ 12÷39-40) በማለት አስጠንቀቃቸው:: በዚህ ሞቱንና በሦስተኛው ቀን መነሣቱን አመልክቷል:: በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶአል:: በቅዱሳት መጻሕፍት መጻፉ እና በሐዋርያት መሰበኩ የትንሣኤውን ጠቃሚነት አስረጂዎች ናቸው::

<u>በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ</u>:

በእርግጥም ያረገው በአካል ነው:: እግዚአብሔር መለኮት አይወርድም ወይም ዐያርግም:: እግዚአብሔር (መለኮት) ከላይም ከታችም በመካከልም፤ በሰማይና በምድር እንዲሁም በሁለቱም መካከል አለ:: ሁሉን የሞላ እና በሁሉም ቦታ የሚኖር ነው:: በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ቅዳሴ ውስጥ (በአካል ወደ ሰማይ ባረግህበት ዕርገትህ ላይ...) እንደምንለው በአካል ወደ ሰማይ ዐርጓል::

ደቀመዛሙርቱ በአካል ሲያርግ አይተውታል «እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው (ሐዋ 1÷9) በእርግጥ ይህ ዕርገት በአካል ነበር ምክንያቱም መለኮትን መመልከት አይችሉም::

ጌታችን በከበረ መንፈሳዊ አካል ወደ ሰማይ ዐርጓል::





ይህ አካል ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልዕክቱ እንደተናገረው እኛ የምንነሣበት መንፈሳዊ አካል ነው፤ «ፍጥረታዊ አካል፣ ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሣል... የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን::» (1 ቆሮ 15÷44፣49):: ይህ እኛ የምንነሣበት መንፈሳዊ አካል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤው ይዞት የተነሣውን አካል የሚመስል ነው «ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል::» (ፊል 3÷21)

የዕርገት ተአምር የመሬት ስበት ኃይል የሚፈታተነው አይደለም:: ይህ ተአምር ለመሬት የስበት ኃይል ክስተት ተገዢ ያልሆነ በከበረ መንፈሳዊ አካል ላይ የሆነ ተአምር ነው::

ለመሬት የስበት ኃይል ተገዢ የሆነው ቁሳዊ አካል ብቻ ነው፤ ስለዚህም ጌታችን ወደ ሰማይ ያረገበት ሰማያዊው አካል ከስበት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሲሆን የመሬት የስበት ኃይልም አልተፈታተነውም ነበር::

እኛም በተመሳሳይ በትንሣኤ ሙታን ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን (1 ተሰ 4÷17) ይህም የመሬት የስበት ኃይል ፈተና አይሆንብትም ምክንያቱም እኛ በምንነሣበት በመንፈሳዊ አካል ላይ የስበት ኃይል ምንም ኃይል የለውም:: ይልቁንም ከትንሣኤው በኂላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ምንኛ ይልቅ!

«ወደ ሰማይ ዐረገ» የሚለው ቃል ወደ ሰማየ ሰማያት ዐረገ ማለት ነው:: ከእርሱ በቀር ወደ ሰማየ ሰማያት ማንም ፈጽሞ ዐላረገም፤ ኤልያስና ሄኖክም እንኳን ቢሆኑ ወደዚህ ዐላረጉም:: ጌታችን ለኒቆዲሞስ፤



www.ethiopianorthodox.org

«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፤ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።» (ዮሐ 3÷13) ብሏልና።

«ሰማየ ሰማያት» የሚለው አገላለጽ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን በሚያንጽበት ወቅት በጸለየው ጸሎት ውስጥ እግዚአብሔርን «በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ! (1 ነገ 8÷27) ባለው ጊዜም ተገልጿል። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥም፤ «እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት! በአርያም አመስግኑት!...ሰማየ ሰማያት አመስግኑት» (መዝ 148÷1-4) ተብሎ ተገልጿል።

በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፤

ይህ እውነት በአዲስ ኪዳን በርካታ ቦታዎች እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ባሉት ትንቢቶች ላይም ተጠቃልሎ ተቀምጦአል።

- (ማር 16÷19) «ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።»
- (ዕብ 8÷1) «ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን።»
- (ዕብ 1÷3) «ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን ወረሰ»
- (ዕብ 12÷2) «ኢየሱስ...እርሱ ነውርን ርቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።»





- (ማቴ 26÷64) «የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ።» ይህ ቃል የተነገረው በሸንጎው ፊት በኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
- (ሐዋ 7÷56): «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።» ይህ ቃል ቅዱስ እስጢፋኖስ በሚወገርበት ጊዜ «መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ሲያይ» የተናገረው ነው።
- (መዝ 110÷1): «እግዚአብሔር ጌታዬን:- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።»

ነገር ግን በእግዘአብሔር ቀኝ መቀመጥ ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ቀኝ ወይም ግራ የለውም ምክንያቱም ቀኝ ወይም ግራ ያለው የተወሰነ ነገር ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ አይወሰንም። ከዚህ ባሻገር በእግዚአብሔር ቀኝ ሌላ አካል እንዲቀመጥ የሚያስችል ቦታ የለም።

እግዚአብሔር ወልድ በአባቱ ቀኝ ቢቀመጥና ይህንም ቦታ ይዞ በመቀመጥ ትርጉም ከተረዳነው «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ አለ።» (ዮሐ 14÷11) የሚለው የጌታችን ቃል ተግባራዊ አይሆንም ነበር።

ታዲያ «ቀኝ» የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የቃላት ስያሜ መሠረት ቀኝ ማለት ኃይልን ቅድስናን ወይም ክብርን የሚያመለክት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ኃይልን ከመግለፅ አኳያ መዝሙረኛው ዳዊት «የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፤ አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ::» (መዝ 118÷15-17) «በቀኝህ አድን አድምጠኝም» (መዝ 60÷5፤108÷6) ብሏል:: ሙሴም በምስጋና መዝሙሩ «አቤቱ ቀኝህ በኃይል ከበረ አቤቱ ቀኝህ ጠላቱን አደቀቀ::» (ዘጸ 15÷6) ብሏል::

ዳግመኛም ቃሉ ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች እንዳከበረበት እና እጁን በታናሹ ራስ ላይ ጭኖ እንዳከበረው ለክብርም ይሆናል:: ይህ ማለትም ታላቅ ክብርን ሰጠው ማለት ነው:: (ዘፍ 48÷17-19) ይህም መዝሙረኛው «ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች» (መዝ 45÷9) ባለጊዜ መናገር የፈለገው ማለት ነው:: በምሳሌያዊ አነጋገር ይህ ቃል ለቅድስት ድንግል የተሰጠውን ክብር ያመለክታል:: በተመሳሳይ ትርጉም መዝሙረኛው፤ «እግዚአብሔር በቀኝህ ነገሥታትን በቁጣው ቀን ይቀጠቅጣቸዋል» (መዝ 110÷5) ብሏል::

በፍርድ ቀንም እግዚአብሔር ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው ያቆማቸዋል ይህ ማለትም ቀኝ ጽድቅንና ክብርን ያመለክታል ማለት ነው:: ስለዚህ የገነትን ቃል ኪዳን በመስቀል ላይ ሆኖ የተቀበለውን ወንበዴ «በጌታችን ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ» ብለን እንጠራዋለን:: በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ የዮሐንስን መወለድ ለዘካርያስ የነገረው የጌታ መልአክም እጅግ ያማረ ማስረጃ ነው:: (ሉቃ 1÷11)

ስለዚህ «የእግዚአብሔር ቀኝ» ማለት የእግዚአብሔር ኃይል፣ ጽድቅ፣ ክብር ማለት ሲሆን «መቀመጥ» ማለት ደግሞ የማይለወጥ የተወሰነ ማለት ነው::





ጌታችን ወደ ሰማይ ሲያርግ ኃይሉ ግርማው እና ክብሩ ልክ እንደ በፊቱ ያልተለወጠ-የተወሰነ ነው:: ይህ ማለት ከምቀኝነት የተነሣ በሐሰት የደረሱበት ነቀፌታዎችና ስድቦች ሁሉ ለምሳሌ:- አሳች መባሉ (ማቴ 27÷62)፤ ሰንበትን አያከብርም መባሉ (ዮሐ 9÷16)፤ አጋንንትን የሚያወጣው በብዔል ዜቡል ነው መባሉ (ማቴ 12÷24)፤ ሳምራዊ ነው ጋኔንም አለበት መባሉ (ዮሐ 8÷48)፤ እነዚህ ሁሉ ነቀፋዎችና ስድቦች ወደ ሰማይ ባረገ እና በአባቱም ቀኝ በተቀመጠ ጊዜ ተደምድመዋል::

በአባቱ ቀኝ መቀመጥ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ (ፊል 2÷7) ተብሎ እንደተጻፈ ራሱን ባዶ ማድረጉ ተጠናቀቀ ማለት ነው:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የሰብዓዊ ባህርይ ድካሞችን ታግሷል፣ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ ደክሞአል እንዲሁም አንቀላፍቶአል:: ነገር ግን በአባቱ ቀኝ ሲቀመጥ እነዚህ ሁሉ ፍጻሜያቸው ሆነ:: የተያዘበት፣ የተሰደበበት፣ የተንገላታበት እና የተሰቀለበት ድካምም ሁሉ ተፈጸመ::

በዳግም ምጽአቱ በኃይልና በክብር ይመጣል::

<u>ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በክብር ይመጣል</u>:

ወደፊት በሚያገኘው አዲስ ክብር ሳይሆን በመለኮታዊ ባህርዩ ባለው ክብር እነሆ ይመጣል:: ዓለም ሳይፈጠር በነበረው ክብር ይመጣል:: (ዮሐ 17÷5) እንዲሁም በበረት ተወልዶ በሥጋ በተመላለሰ ጊዜ በተወው ነገር ግን ወደ ሰማይ ሲያርግና በአባቱ ቀኝ ሲቀመጥ በመለሰው ክብሩ ይመጣል:: ስለዚህም ራሱ «የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ይመጣል::» (ሉቃ 9÷26) ብሏል::



www.ethiopianorthodox.org

«በክብሩ ይመጣል» የሚለው ቃል ምንኛ ድንቅ እና ታላቅ ነው፣ ይህም ቃል «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያንጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል» (ማቴ 16÷27) ተብሎ ተደግሞአል:: የአባቱ ክብር የእርሱ ክብር ነው የእርሱ ክብርም የአባቱ ክብር ነው:: ምክንያቱም ከመለኮታዊ ክብር አኳያ እርሱና አባቱ አንድ ናቸው::

ዳግመኛ የሚመጣው ለፍርድ ነው:: ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበው ዘንድ ይመጣል:: ይህ ቃል በማቴዎስ 25 ውስጥ፤ «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል:: አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል::» (ማቴ 25÷31-33) ተብሎ ተደግሞአል::

ለፍርድ ለሚመጣበት ለዚህ ጊዜ በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ::» (ራዕ 22÷12) ማለቱ ማረጋገጫ ነው::

የእርሱ ለፍርድ መምጣት የዓለም መጨረሻ ይሆናል::

በስንዴውና በእንክርዳዱ ምሳሌ ውስጥ፤ «መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፤ አጫጆቹም መላእክት ናቸው:: እንግዲህ እንክርዳዱ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል:: የሰው ልጅ መላእክቱን





ይልካል፤ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃውንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል::... በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ::» (ማቴ 13÷39-43)

ለፍርድ በሚመጣበት በዚህ ዳግም ምጽአት አጠቃላይ ትንሣኤ ይሆናል::

«በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ::» (ዮሐ 528-29):: ስለዚህ ዳግም ምጽአቱ በአጠቃላይ ትንሣኤ፣ በፍርድ እና በዓለም መጨረሻ የታገዘ ነው::

በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርዳል፤ ይህም ማለት፣ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ሕያዋን ሆነው በሚቀሩትና እንዲሁም በሚሞቱትና በሚነሡት፣ መልካም ወይም መጥፎ በሰሩት ላይ ይፈርዳል:: ሐዋርያውም ስለ እርሱ ፍርድ፤ «መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል::» (2 ቆሮ 5÷10) ብሏል::

ጸሎተ ሃይማኖት እንደሚለው በዚህ የፍርድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜ በሌለው መንግሥቱ ይመጣል::

ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም:

የነቢዩ ዳንኤል ትንቢት፣ «ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው:: መንግሥቱም የማይጠፋ ነው::» (ዳን 7÷14) ይላል:: መጨረሻ ከሌለው ከዚህ መንግሥት መልአኩ ገብርኤል ለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ...በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም



www.ethiopianorthodox.org

ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም::» (ሉቃ 1÷31-33) አላት::

የእርሱ መንግሥት በጊዜ የተወሰነ ምድራዊ መንግሥት ሳይሆን መንፈሳዊ መንግሥት ነው::

ይህ መንግሥት በጌታችን ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ የፈለገውና «አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» (ሉቃ 23÷42) ሲል የተናገረው መንግሥት ነው:: መንግሥቱም ለዘመናት ከሰዎች ርቆ ስለነበር ከብዙ ትውልዶች በኋላ ጌታችን ለወንበዴው፤ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ፤» (ሉቃ 23÷43) አለው::

ገነት የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረሻ ስጦታ ናት ስለዚህ ወደገነት የገባ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባል::





## ምዕራፍ ሦስት

ቀጥሎ ያለው የጸሎተ ሃይማኖት ክፍል ስለመንፈስ ቅዱስ የሚያትት ነው::

[በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሠጥ፤ ከአብ የሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን::]

በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን:

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሕያው እንደሆነ እናምናለን:: መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር አብ እና የእግዚአብሔር ወልድ መንፈስ ነው::

የእግዘአብሔር መንፈስ በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ:- ቅዱስ ነው:: ስለዚህ ጌታችን ምስጢረ ክህነትን ለደቀመዛሙርቱ ሲሰጣቸው፣ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው::» (ዮሐ 20÷22፣23):: አገልግሎታቸውን ስለመጀመራቸውም «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ::» (ሐዋ 1÷8)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ጳጳሳትም «መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::» (ሐዋ 20÷28) ሲላቸው በሮም ላሉት አይሁድ ደግሞ «መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን መልካም



www.ethiopianorthodox.org

ተናገረ::» (ሐዋ 28÷25) ሲል ተናገረ::

አንዳንድ ጊዜ «መንፈስ» የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስን ይወክላል::

የዚህ ምሳሌዎች:-

- «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ» (ራዕ 2÷29፤3÷6፤13፤22):: እዚህ ላይ መንፈስ የተባለው በእርግጥም የእግዚአብሔር መንፈስ ነው::
- ጌታችን ስለጥምቀት ለኒቆዲሞስ የተናገረው ቃል፣ «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም::» (ዮሐ 3÷5) ይላል:: ጌታችን ይህን ሲናገር ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል ማለቱ ነው::
- በ(1 ቆሮ 12) የተገለጹት የመንፈስ ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያረጋግጠው መንፈስ ቅዱስ የጌታ መንፈስ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ ነው::
- (ኢሳ 61÷1): «የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው...እግዚአብሔር ቀብቶኛልና::»
- (2 ቆሮ 3÷17): «ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ::
- (ሕዝ 36÷27): «መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትዕዛዜም አስሄዳችኋለሁ፤»
- (ኢዩ 2÷28): «መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ፤»
- (መዝ 139÷7): «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት





እሸሻለሁ?»

(መዝ 51÷11): «ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ::»

መንፈስ ቅዱስ የአባቶች መንፈስ መሆኑ በተከታዮቹ ጥቅሶች በግልጽ ተቀምጧል:: ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ የተናገረው ቃል፤ «በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም፤» (ማቴ 10÷20) ይላል:: (ማር 13÷11) ፤ እና (ሉቃ 12÷12)ን ተመልከት::

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መንፈስ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሆኑ ተረጋግጦአል::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ «የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ::» (ገላ 4÷6) ብሏል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር:: (1 ጴጥ 11÷1) አለ::

መንፈስ ቅዱስ የአብ መንፈስ እና የወልድ መንፈስ መሆኑ ያለምንም ጥርጥርም የቅድስት ሥላሴን አንድነት በግልፅ ያሳያል::

የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት:

የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት መቅዶንዮስ ክዶአል፤ በዚህ ምክንያትም ከክ.ል. በኋላ በ381 ዓ.ም ቁስጥንጥንያ ላይ በተካሄደው ሁለተኛው ሃይማኖታዊ ጉባኤ ተወግዞ ተለይቷል:: ይሄው ሃይማኖታዊ ጉባኤ ታዲያ



www.ethiopianorthodox.org

የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በጸሎተ ሃይማማት ውስጥ በሚከተለው ዓረፍተ ነገር ወስኖ አስቀምጦታል:: (በመንፈስ ቅዱስ በእውነት እናምናለን፤ እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሠጥ ከአብ የሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን::) እዚህ ላይ «ጌታ» የሚለው ቃል «እግዚአብሔር» ማለት ነው::

- የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የሰጺራ ባል የሆነውን ሐናንያን በመገሠጽ በተናገረበት ቃል ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል «መንፈስ ቅዱስን ታታልል ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ... እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም::» ሲል (ሐዋ 5÷3-4)

- በተመሳሳይም መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የሚያድር መሆኑን (ማደሩን) በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ቃል በግልጽ የተቀመጠ ነው::

ይኼውም ጳውሎስም «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?» (1 ቆሮ 6÷19) ሲል በ(1ቆሮ 3÷16) ደግሞ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን?» ይላል:: በነዚህ ጥቅሶች ቅዱስ ጳውሎስ አንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ በሌላ ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ማለቱ አንድ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው::

- የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት «ጌታ መንፈስ ነው» (2 ቆሮ 3÷17) በሚለው ቃል ተረጋግጦአል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለሳምራዊቷ ሴት «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፣» (ዮሐ 4÷24) ባላት





ጊዜ ይህ ተረጋግጧል:: እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ እግዚአብሔር አባት፣ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሁም እግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ነው::

- የእግዚአብሔር የመፍጠር ኃይል የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ማረጋገጫ ነው::

የመፍጠር ኃይል የእግዚአብሔር ባህርይ ብቻ ነው፤ መዝሙረኛው፤ «ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ::...ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉም:: ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ:: መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም:: (መዝ 104÷27-30) እንዳለ::

- የመንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ መሆን ሌላው የአምላክነቱ ማረጋገጫ ነው::

መዝሙረኛው ዳዊት፣ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ» (መዝ 139÷7-8) አለ:: በሁሉ ቦታ መሆንና መገኘት የእግዚአብሔር ባህርይ ብቻ ነው::

- ለሰዎች የተሰጡት ሥጦታዎች የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ያሳያሉ::

በመጀመሪያዩቱ የቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ፣ «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፣...አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል:: ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን



www.ethiopianorthodox.org

መናገር ይሰጠዋል:: ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ ለአንዱም ትንቢትን መናገር... ይሰጠዋል:: ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል::» (1 ቆሮ 12÷4-11) ብሏል::

- የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ሌላው ማስረጃ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም መንፈስ ያለው መሆኑ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ...» (ዕብ 9÷10) ይላል:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው ዘላለማዊነትም የእግዚአብሔር ብቻ የሆነ ባህርይ ነው:: ይህ ጥቅስ ታዲያ የክርስቶስ እና የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ማረጋገጫ ነው::

- ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ማረጋገጫ ነው::

<u>ሕይወትን የሚሰጥ</u>:

መንፈስ የሕይወት ምንጭ መሆኑ የታወቀ ነው ስለዚህ እርሱ ሕይወትን የሚሰጥ ነው:: ይህም እግዚአብሔር አጥንቶችን በማስነሳቱ ሂደት ውስጥ ተረጋግጧል:: (ሕዝ 37):: ነቢዩ ሕዝቅኤል፤ «የእግዚአብሔር እጅ በላዬ ነበረ እግዚአብሔርም በመንፈሱ አወጣኝ አጥንቶችም በሞሉበት ሸለቆ መካከል አኖረኝ::...እርሱም የሰው ልጅ ሆይ እነዚህ አጥንቶች በሕይወት ይኖራሉን? እኔም:- ጌታ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ታውቃለህ አልሁ::...ትንፋሽም ገባባቸው ሕያዋንም ሆኑ፤» (ሕ 37÷1-3፣10)





ሲል እግዚአብሔርም፤ «መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፤» (ሕዝ 37÷14) ብሏል::

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ በተመሳሳይ መልኩ ስለተገደሉት ስለሁለቱ ምስክሮች፤ «ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው፤ በእግሮቻቸውም ቆሙ፤» (ራዕ 11÷11) ይላል:: ጌታም በእውነት፤ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው::» (ዮሐ 66÷3) አለ:: ዳግመኛም ለሙታን ሕይወት የሚሰጥ አምላክ ነው::» (ሮሜ 4÷17) «ሁሉን በሕይወት የሚጠብቅ እግዚአብሔር ነው፤» (1 ጢሞ 6÷13) ተብሎ ተጽፏል::

በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንደሆነ ጥርጥር የለውም:: መንፈሱን በውስጣቸው ያሳድራል እነርሱም በሕይወት ይኖራሉ:: (ሕዝ 37÷14) ይህም ጸሎተ ሃይማኖት እንደሚያስተምረን የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው:: ጸሎተ ሃይማኖት መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረፀ መሆኑንም አስተምሮናል::

<u>ከአብ የሠረፀ</u>:

«ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ» (ዮሐ 15÷26) የሚለው ቃል ጌታችን ስለመንፈስ ቅዱስ በተናገረበት ወቅት የተባለ ነው::

ይሁንና የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ ወንድሞቻችን በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ ከወልድም የወጣ (የሠረፀ) የሚለውን ጨምረውበታል::

ይህ ጭማሪ በቤተ ክርስቲያን መካከል እስከአሁን ድረስ ቀጥሎ ያለውን መከፋፈል አስከትሎአል::



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ ይመጣል» (ዮሐ 15÷26) «እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ:: (ዮሐ 16÷7) ማለቱ እውነት ነው:: ሆኖም ግን የሚከተለውን ማወቅ አለብን::

በመሥረጽ እና በመላክ መካከል ታላቅ የሆነ ሥነ መለኮታዊ ልዩነት አለ:: መላክ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከናወን ሲሆን መሥረጽ ግን ዘላለማዊ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን በበዓለ ሃምሳ ዕለት ለሐዋርያት ልኮላቸዋል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ነበረ፤ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: በፍጥረት ታሪክ ውስጥ፤ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ:: ምድርም ባዶ ነበረች:: አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም፤ በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር::» (ዘፍ 1÷1-2) ተብሏል:: ዳግመኛም መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሠራውና በነቢያት እና በሌሎች ላይ እንዴት እንደወረደ ይነግረናል::

የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ ወረደ ትንቢትም ተናገረ:: (1 ሳሙ 10÷10) የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ:: (1 ሳሙ 16÷14):: ዳግመኛም የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ መጣ:: (1 ሳሙ 16÷13):: ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ ከነቢዩ ሕዝቅኤል ጋር ስለሠራው ይነግሩናል:: (ሕዝ 341) ስለ እግዚአብሔር መንፈስ በርካታ ጽሑፎችም በነቢዩ ዳዊት መዝሙር ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ::





በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዲሁም ከክርስቶስ መወለድ በፊት በሁለቱ ኪዳናት መካከል በነበረው ዘመን መንፈስ ቅዱስ ስለሠራው ሥራ ብዙ ማለት ይቻላል::

የዮሐንስ ልደት በተበሠረበት ጊዜ ስለ እርሱ፤ «ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል (ሉቃ 1÷15) ተብሏል:: ስለእናቱ ስለ ኤልሣቤጥም መንፈስ እንደሞላባት» (ሉቃ 1÷41) ተነግሯል:: አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ:: (ሉቃ 1÷67) ::

መልአኩም የጌታችንን መወለድ ለቅድስት ድንግል ማርያም ሲያበስራት፤ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤» (ሉቃ 1÷35) አላት:: ስለቅድስት ድንግል ማርያም መልአኩ ለአናጺው ለዮሴፍ፤ «ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነው::» (ማቴ 1÷20) አለው:: ስለአረጋዊው ስምዖንም፤ «ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር ጻድቅና ትጉህም ነበረ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ:: በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር::» (ሉቃ 2÷25-26) ተብሏል::

ስለዚህ በጰራቅሊጦስ ዕለት በደቀመዛሙርቱ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ መላኩ ከዘላለም ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከመስረፁ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም::

መንፈስ ቅዱስ ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በቅድስት ሥላሴ ውስጥ ሕይወትን የሚወክለው አካል እርሱ ሲሆን እግዚአብሔርም በእርሱ መንፈስ ይኖራል:: መንፈስ ቅዱስም ከዘለዓለም አስቀድሞ እና ጌታችን



www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ ቅዱስን የላከላቸው ደቀመዛሙርት ከመወለዳቸው በፊት ከአብ የሠረፀ ነው::

ለምሳሌ:- ስለ እግዚአብሔር ወልድ መወለድ፤ «ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ:: ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ::» (ገላ 4÷4-5) ተብሏል::

የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ወደ ዓለም ቢላክም ግን የእግዚአብሔር ልጅ ከዘላለም ጀምሮ ከአብ የተወለደ ነው፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም (ዮሐ 1÷3):: ስለዚህ ከዘላለም ጀምሮ መወለዱ አንድ ነገር ሲሆን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ መላኩ ደግሞ ሌላ ልዩ ነገር ነው:: ስለመንፈስ ቅዱስም ተመሳሳዩን ማለት እንችላለን ከዘላለም ጀምሮ ከአብ መሥረፁ አንድ ነገር ሲሆን በጰራቅሊጦስ ዕለት ለደቀመዛሙርቱ መላኩ ደግሞ ሌላ የተለየ ነገር ነው::

አንዳንዶቹ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አካል ወይም ከአብ የተላከ በመሆኑ ከአብና ከወልድ በደረጃ ያንሣል ብለው ቢያስቡም ጸሎተ ሃይማኖት [ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን] የሚለውን ቃል ጨምሮ ይዟል::

እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን:

የእግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ እንሰግድለታለን ከአብና ከወልድ ጋርም በእኩል ደረጃ እናመሰግነዋለን::

በጸሎቶቻችን መጨረሻ ላይ «ምስጋና ይሁን አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ» እንላለን:: እያንዳንዱን ጸሎታችንንም «በአብ





ስም በወልድ ስም በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ አሜን::» በሚል ቃል እንጀምራለን::

የመንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ መላክ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ክርስቶስ በክብር በሥልጣን ያንሣል ማለት አይደለም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ፤ «አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል::» (ኢሳ 48÷16)፤«የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው...እግዚአብሔር ቀብቶኛልና::» (ኢሳ 61÷1) ይላል:: ይህ ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥልጣን በክብር ከመንፈስ ቅዱስ ያንሣል ማለትም አይደለም:: አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቃቸው አዝዟል:: (ማቴ 28÷19)

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በመጀመሪያው መልእክቱ፤ «የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ::» ብሏል::

በረከት የሚገኘው በሦስቱ አካላት በአንድነት ነው፡

በረከት የሚገኘው በሦስቱ አካላት በአንድነት ነው:: (2 ቆሮ 13÷14) ላይ ባለው ትምህርት መሠረት «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን:: አሜን::» እንላለን::

«ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እናመሰግነዋለን» የሚለው የጸሎተ ሃይማኖት ቃል በሦስቱ አካላት መካከል ያለውን እኩልነት ያመለክታል::

ሦስቱ አካላት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርያት እኩል ናቸው:: እያንዳንዱ አካል ዘላለማዊ፣ ፈጣሪ፣ በሁሉ የሚገኝ፣ ወሰን የሌለው



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን ቻይ፣ ሲሆን በሌሎችም በእያንዳንዱ ገጽታ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ነው:: ይሁንና ወልድን ከዘመናት በፊት የተወለደ ስንለው መንፈስ ቅዱስንም እንዲሁ ከዘመናት በፊት ከአብ የሠረፀ እንለዋለን::

ወደአብ እንደምንጸልይ ሁሉ ወደ ወልድና መንፈስ ቅዱስም እንጸልያለን:: በየሰዓቱ በምንጸልያቸው ጸሎቶች እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ የሚሆኑ በርካታ ምሳሌዎች አሉ:: ለአብ የሚደርሱ ጸሎቶች ብዙዎች በመሆናቸው በግልጽ ይታወቃሉ:: ለወልድ (ለእግዚአብሔር ልጅ) ከቀረቡት ጸሎቶች፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትነትን ሲቀበል የጸለየው ጸሎት ሲሆን፤ እርሱም፤ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል» (ሐዋ 7÷59) ሲል የጸለየው ነው::

ወደ መንፈስ ቅዱስ ለሚደረጉት ጸሎቶች ምሳሌ የሚሆነው [ሰማያዊ ንጉሥ የሆንህ የእውነት መንፈስ ሆይ በሁሉ ሆነህ ሁሉን የምትሞላ...በምህረትህ እንድትጎበኘን እንጠራሃለን] የሚለው የሦስት ሠዓት ጸሎት ነው::

ዳግመኛም ጸሎተ ሃይማኖት ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል::

<u>በነቢያት የተነገረ</u>:

ይህ ቃል በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ ቃል በግልጽ ተቀምጧል፤ «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ::»





ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለአይሁድ፤ «መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን መልካም ተናገረ::» (ሐዋ 28÷25) አላቸው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ «የሚነግረው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤» (ማር 13÷11) ብሏቸዋል:: ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፤» (1 ቆሮ 2÷13) አለ:: ይህ ቃል ደግሞ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ፤ «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፤» (ዮሐ 14÷26) ያለውን ቃል ያስታውሰናል::

ለብዙ ጊዜያት መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ ዳዊት አንደበት ተናግሯል:: ይህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ «ጻፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ? ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ:- ጌታ ጌታዬን:- ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው፤» (ማር 12÷35-36) (ማቴ 22÷43-44) (መዝ 110÷1) ተብሎ ተገልጿል::

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ አስቆሮቱ ይሁዳ፤ «ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር:: (ሐዋ 1÷16) ብሏል::

«በነቢያት የተነገረ» የሚለው ቃል መለኮታዊ መነሳሳትን ያመለክታል:: ሐዋርያው ስለዚህ ሲናገር «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ...ይጠቅማል::» (2 ጢሞ 3÷16) አለ:: ይህ መነሣሣት ከእግዚአብሔር እንዴት ሊመጣ ቻለ? ይህ መነሣሣት የመጣው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሲሆን ይህም ሌላው የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ማረጋገጫ ነው::

በዚህ ቅዱስ ሥሉስ ላይ የሚያተኩረውን የጸሎተ ሃይማኖት ክፍል አጠናቀቅን:: ቤተክርስቲያንን፣ ጥምቀትን፣ ዳግም ምፅአትን እና የሚመጣውን ዘመን ሕይወት ወደሚመለከተው ክፍለ-ትምህርት እንሸጋገራለን::





## ምዕራፍ አራት

ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሩዋት በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን::

ቤተክርስቲያን:

ጸሎተ ሃይማኖት [ቅድስት በምትሆን በአንዲት ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን እናምናለን] ይላል:: ጸሎተ ሃይማኖት ላይ የተጠቀሰችው ያቺ ቤተክርስቲያን ማን ናት? ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ነገሮችን ያመለክታል::

ሀ) የቤተክርስቲያንን ህንፃ

ለ) ምዕመናንን

ሐ) የቤተክርስቲያን መሪዎችን ወይም ካህናትን፣

- ቤተክርስቲያን እንደ ሕንፃ

ጵርስቅላንና አቂላን በማመልከት “በቤታቸውም ላለች ቤተክርስቲያን” (ሮሜ16:5) እና “እኔም በየስፍራው በየአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር” (1ቆሮ 4:17) በሚለው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ውስጥ ይህ በተናጠል ተቀምጧል::

- ቤተክርስቲያን እንደምዕመን

ጸሎተ ሃይማኖት “አንዲት ቤተክርሰቲያን” ሲል የቤተክርስቲያን ሕንፃ ማለቱ ሳይሆን ምዕመናን ማለቱ ነው:: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ መጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን “ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር:: (ሐዋ 2:47) “በዚያ ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች



www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ።" (ሐዋ 8፡1) ሲል ይናገራል። ይህን ማለቱ በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞችን ማለቱ ነው። ዳግመኛም "ጴጥሮስም በወሕኒ ይጠበቅ ነበር። ነገር ግን በቤተክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር"። (ሐዋ 12፡5) ተብሏል። ይህም ማለት ክርስቲያኖች ለእርሱ ይጸልዩ ነበር ማለት ነው። በተመሳሳይ መልኩ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "መጀመሪያ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ እሰማለሁ" (1 ቆሮ፡ 11፡18)እንዲሁም "ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አጽንቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። "(ኤፌ 5፡25፣26)፣ እዚህ ላይ ቤተክርስቲያን ማለት በተሰበከውና የእምነት መሰረት ሆኖ በተነገረው ቃል ተጠምቀው ለመቀደስና ለመንጻት የተሰቀለላቸው የኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች ማለትም ነው።

- ቤተክርስቲያን እንደመሪ (ክህነት)

ምክርን በተመለከተ፣ "እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ደግሞም ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንልህ።" (ማቴ 18፡17) ተብሎ ተጽፏል።

እዚህ ላይ "ቤተክርስቲያን" ማለት የቤተክርስቲያን አመራር ማለት እንጂ ሁሉንም ምዕመኖቿን ማለት አይደለም። ለዚህም ያንኑ ቃል ተከትሎ ወዲያውኑ፣ "እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል"። (ማቴ 18፡18) ተብሎ ተጽፏል።





ስለዚህ በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ "ቤተክርስቲያን" ተብሎ የተገለጸው ቃል አማኞች እና አመራሮቻቸው ማለት ነው። በመቀጠልም ጸሎተ ሃይማኖት የቤተክርስቲያንን ሁኔታዎች (ባሕርያት)ያብራራል።

<u>አንዲት ቤተክርስቲያን፡</u>

ቤተክርስቲያን በእምነት፣ በዶግማ፣ በአስተምህሮ እና በመሠረተ እምነት እንዲሁም በመንፈሳዊነት አንዲት ናት። የኤፌሶን መልዕክት "በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፤...."(ኤፌ 4፡42፣) ቤተክርስቲያን በእምነት እና በዶግማ እንዲሁም በትምህርት፣ በሥነ መለኮታዊ ጽንሰ ሐሳቦች አንድ በመሆኗ ማንም ከዚህ እምነት የሚያፈነግጥ ሁሉ በቤተክርስቲያን አማካይነት ከቤተክርስቲያን አባልነቱ የተወገደ ሲሆን፣ ቤተክርስቲያን ግን በእምነት አንድ ሆና የጸናች ናት።

ጌታችን ስለ ራሱ ከአብ ጋር በተነጋገረበት ቃል ውስጥ፤ "ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ በቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ....እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፤፡ (ዮሐ 17፡20-22) ብሏል።

ስለ ቤተክርስቲያን አንድነትም ኢየሱስ ክርስቶስ፤"ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጐች አሉኝ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምጼንም ይሰማሉ፤ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ።" (ዮሐ 10፡16) አለ። ይህ አንድ እረኛ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጐቹ ይሰጣል"። (ዮሐ10፡11) ሲል የተናገረው ኢየሱስ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ነው።

ቤተክርስቲያን አንድ አካል እንደመሆኗ የዚህ አካል ራስም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሆኑ ቤተክርስቲያን አንዲት ናት።

ይህም በመልዕክታቱ ውስጥ፤ "ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው"። (ኤፌ 5:23) "እርሱም አካሉ ማለትም የቤተክርስቲያን ራስ ነው፤ (ቈላ 1:18)፤ አካሉም ማለት ቤተክርስቲያን፤ (ቈላ1:24) ተብሎ ተጽፏል። ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል አንድ ስለሆነ እኛ ሁላችንም ሐዋርያው፤ "የአካሉ ብልቶች ነን" (ኤፌ 5:30) እንዳለ የአካሉ ብልቶች በመሆናችን ቤተክርሰቲያን አንዲት ናት።

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ስለሆነች አንዲት ናት።
መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፤ ነገር ግን ከእርሱ በፊት ተልኬያለሁ። ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው ቀድሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል።"(ዮሐ3:28-29) አለ። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቃል በ(ኤፌ 5:31) ላይ ተገልጿል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዲት ሙሽራ እንዳለችው ግልፅ ነው። እርስዋም ቤተክርስቲያን ናት፤ ሐዋርያው፤ "እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ "(2ቆሮ:11:2) ብሎ እንደተናገረው። በእግርጥም የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ አንዲት ናት እርሷንም በተመለከተ በመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ ውስጥ "ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት፤(መኃ 6:4) ተብሎ በምሳሌ ተገልጿል።





ቤተክርስቲያን አንዲት ከሆነች ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "አብያተ ክርስቲያናት" ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ምንን ለመግለፅ ነው? "አብያቶ ክርስቲያናት" የሚለው ቃል አንዱን ከሌላው ለመለየት ቤተክርሰቲያን የተመሠረተችበትን ቦታ ለመግለፅ የሚያገለግል ነው።

ስለዚህም "በይሁዳም ሆነ በገለሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተክርስቲያናት በሠላም ኖሩ፣ ታነጹም በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።" (ሐዋ:31) ተብሏል።

በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ውስጥም በእስያ ስላሉት ስለ ሰባቱ አብያተክርስቲያናት የተፃፈውን ሰምተናል፤ "በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ሰምርኔስ ወደ ጴርጋሞንም ወደ ትያጥሮንም ወደ ሰርዴስም ወደ ፊልድልፍያም ወደ ሎደቅያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተክርስቲያናት ላክ። "(ራዕ 1:11)

ይሁንና እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የአንዲት ቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው፡፡

ቤተ ክርስቲያን በምድር እና በሰማይ አንዲት ናት፡፡
በሰዎች መካከል በሆነችው በእግዚአብሔር ድንኳን ከእነርሱም ጋር እግዚአብሔር በሚያድርባት በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ሁሉም በአንድነት ይሰበሰባሉ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፡፡ (ራዕ 11፡ 2:3)

እነዚህ አንድ ህዝቦች ወይም አንዲት ቤተ ክርስቲያን፤ መንግስተ ሰማያትን የሚወርሱት ሁሉም የአማኝ መንጋዎች፤ በባለራዕዩ



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ዮሐንስ ታይተዋል፤ እርሱም አለ፤ "ከዚህ በኋላ አየሁ እነሆ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ ነጭ ልብስም ለብሰው … እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፡፡ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ" (ራዕ 7፡9-14)::

በሰማይ ያለችው ይህቺ አንዲት ቤተክርስቲያን መላእክትንም ታጠቃልላለች፡፡ ይህቺ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን መላእክትን እና በሕይወተ ሥጋ የተለዩትን የቅዱሳን ሰዎች ነፍሶች እና እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚያልፉትን ሰዎች ነፍሶች አቅፋ ትይዛለች ሁሉም መላዕክትና ሰዎች የእግዚአብሔር ፍጡሮች፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ ዜጎች እና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናቸው፡፡ (ኤፌ 2፡19)

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣

ስለዚህች ቤተክርስቲያን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፤ "እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ"፡፡ (1 ጴጥ 2፤5)፤ እና "የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1 ጴጥ 2፤9) ሲል ተናገረ፡፡

ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተቀደሰች ናት፡፡ የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን" (ራዕ 1፡5) ይላል፡፡ በመጀመሪያዪቱ የዮሐንስ መልእክትም ስለ እግዚአብሔር አብ





"የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡" (1ዮሐ1፡7) ሲል መዝሙረ ዳዊትም "በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ" (መዝ 51፡7) ይላል፡፡ ይህ ሂሶጵ በብሉይ ኪዳን ከነበረው የደም መሥዋዕት መረጨት (መነከር) በኋላ ለማንጻት እና ለካህ የሚያገለግል ነበር፡፡

ቤተክርስቲያን በጥምቀት የተቀደሰች ናት፤

በጥምቀት አሮጌው ሰው ሞቷል ቅዱስ እና በኢየሱስ ክርስቶስ አምሳል የሆነው አዲስ ሰው ደግሞ ይነሳል፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፡፡" (ገላ 3፡27) እንዳለው ይህ ማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ቅድስና፣ ጽድቅ እና ንጽህና ለብሰቻኋል ማለት ነው፡፡ ዳግኛም ይኼው ሐዋርያ "ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለእርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ:: እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ (ኤፌ 5፡25-27) ሲል ያስረዳል::

ቤተክርስቲያን በተቀደሰው የሜሮን ምስጢር የተቀደሰች ናት:: በተጠመቁት ሰዎች ላይ በሚያድረው በመንፈስ ቅዱስ ይቀደሱ ዘንድ ለሚቀቡት እንዲሁም ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ቤተመቅደሶች ለሚሆኑት ሰዎች በሚፈጸመው በምስጢረ ሜሮን ሥርዓት ውስጥ በሚጠመቁ ሰዎች ላይ በሚያድረው በመንፈስ ቅዱስ ይቀደስ ዘንድ እንዲሁም የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደሶች ይሆኑ ዘንድ የሚቀቡበት በቅዱስ ሜሮን ይቀባ



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ አንድ ሰው በምስጢረ ሜሮን ሥርዓት ይቀባ ዘንድ ያስፈልገዋል። ልክ ሐዋርያው "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?(1ቆሮ3:16)፤"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀባላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? "(1ቆሮ 6:19)፤ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ።" (1ቆሮ 3:17) ያለበትና እንዲሁም "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን" (1ቆሮ:15) ያለበት ነው። ይህ የሚያረጋግጠው ደግሞ ሥጋ ቅዱስ እንደሆነ ነው።

ቤተክርስቲያን የአማኞች ስብብስብ ስትሆን አማኞችም በሐዋርያት ዘመን ቅዱስ ተብለው ተጠርተዋል።

ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ፤ ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሠላምታ አቅርቡ (ፊል 4:21) ካለ በኋላ በኤፌሶን ለነበሩ ቅዱሳንም "በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን" በማለት (ኤፌ 1:1) በክርስቶስ ሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን" (ኤፍ 1:3፤1) በማለት ተናግሯል።

ለዕብራውያን በላከው መልዕክቱም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች" (ዕብ 3:1) በማለት ተናግሯል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ድልን ያደረጉ "ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ስራህ ታላቅና ድንቅ ነው...የአሕዛብ ንጉስ ሆይ!(ራዕ 15:3) በማለት ይዘምራሉ። በዳግም ምጽዓትም ጌታችን





"ከአዕላፋት ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል"(ይሁ 14)። ስለዚህ ሐዋርያው፣ "ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስን ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጐ ልባችሁን ያጽና" (1ተሰ 3:13) አለ።

ቤተክርስቲያን ከቅድስና አኳያ የእግዚአብሔር አርአያ በመሆኗ ቅድስት ናት። ጌታችን "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" (1 ጴጥ 1:16)፣ "በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍፁም እያደረግን"(1ቆ 7:1)፤ "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና" (1 ተሰ 4:3) ሲል ተናግሮናል።

ቤተክርስቲያን ቅዱስ እንደመሆኗ ማንም ኃጢአተኛ ሊገባባት አልተፈቀደም፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር፤ "ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት" (1ቆሮ 5:13)አለ። ይህንንም ሲያብራራ "ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣኦትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካራም ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እፅፍላችኋለሁ። እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ" (1ቆሮ 5:11) ብሏል።

ይህ ቃል ደግሞ ከትክክለኛው እምነት የሚያፈነግጡትን ሁሉ ይመለከታል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና (2ዮሐ1:10-11) ሲል እንደተናገረው። ስለዚህ ቤተክርሰቲያን ከሀዲያንን ከእርሷ አባልነት ለይታለች። ተወግዞ የመለየት



www.ethiopianorthodox.org

ፍርድ በእንደነዚህ አይነት ሰዎች ላይ ይፈጸማል። ከአማኞች ህብረትም ይለያሉ። ምክንያቱም የእምነቱን የትምህርት መሰረት አልተቀበሉትም ዝም ተብለው እንዲቀጥሉ ከተደረጉም ከመሠረተ እምነቱ ማፈንገጣቸውንም በቤተክርስቲያኒቱ አባላት ላይ ማሠራጨታቸውን ይቀጥላሉ። በምድር ላይ ባለችው ቤተክርስቲያን ቅድስና እንደሚያስፈልግ ሁሉ በሰማያዊቷ ቤተክርስቲያንም እንዲሁ ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር ከተማ ስለሆነችው ስለ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም "ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም" (ራእ 21:27) ተብሏል። በእርግጥ በምድርም ሆነ በሰማይ ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው? ፅድቅስ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለው? (2ቆሮ 6:14) ቤተክርሰቲያን በሕይወቷ እና በመንፈሳዊነቷ፤ በትምህርቷ እና በሥርዓቷ በአመራሯ እና በህዝቦቿ ... በሁሉም ነገር ቅድስት ናት።

<u>ዓለም አቀፋዊት ቤተክርስቲያን:</u>

ቤተክርስቲያን ሁሉንም አማኞች በእምነት አንድነት ውስጥ በአንድ ላይ በመሰብሰብ ዓለም አቀፋዊት ናት።

ይህቿ ዓለም አቀፋዊት ቤተክርስቲያን ሁሉንም አጥቢያ አብያተክርስቲያናት በአንዲት ቤተክርስቲያን፤ በአንድ ጸሎት፣ ሃይማኖት፤ እና ወጥ በሆኑ የቤተክርስቲያን ሕጐች አቅፋ ይዛለች። አጥቢያ አብያተክርስቲያናት እያንዳንዳቸው ተለያይተው በውቅያኖስ ውስጥ እንደሚኖሩ ደሴቶች ሳይሆኑ ሁሉም አንዲት ዓለምአቀፋዊት ቤተክርስቲያንን የሚፈጥሩ ናቸው። ይህቿ አለምአቀፋዊት ቤተክርስቲያን





ሁሉንም አማኞች በቅዱስ ቁርባን፣ በአንዲት እምነት፣ በቅዱስ ምስጢራት፣ እንዲሁም በአንድነት አቅፋ ይዛለች።

<u>ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን:</u>

ሐዋርያዊት የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞችን ያመለክታል።
እነርሱም፡- የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን በሐዋርያት የተመሰረተች መሆኗን ለማሳየት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ቤተክርስቲያን የሐዋርያትን ትምህርትን የምትከተል እንጂ ትምህርታቸውን የማትቃረን መሆኗን ለማመልከት ነው።

ሐዋርያው የተናገረውም ይኼንኑ ነው፤ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል። የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" (ኤፌ 2:20) ይህ የሐዋርያት መሠረት ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉት ትምህርት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት፤ "እንግዲህ ሂዱ አሕዛብን ሁሉ... ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው"(ማቴ 28:19፤20) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፤ "ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና" (1ቆሮ:11:23) ብሏል።

ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉትን ትምህርት በመልዕክቶቻቸው በቤተክርሰቲያን ሕይወት እንዲሁም በሕጐቻቸው እና በትምህርቶቻቸው አሳልፈው ሰጥተውናል።

ይህም ትምህርት ቤተክርስቲያን ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ተቀብላ የምታስተላልፈው ሐዋርያዊ ትውፊትም ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ



www.ethiopianorthodox.org

ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ፤ "ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" እንዳለው።

በወረቀትና በቀለም ያልተጻፉ አፍ ለአፍም እየተነገሩ እንደትውፊት የተቀበልናቸው ብዙ ነገሮች አሁንም ድረስ አሉ (2ዮሐ 12፤ 3 ዮሐ 13፤14)። በተጨማሪም፤ በሐዋርያት ዘመን የነበረው የቤተክርስቲያን ሕይወት (ሥርዓትም) ለእኛ ተላልፎልናል። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን በዘመኑ የነበረው የቅዳሴ ሥርዓት፣ የሚያጠምቁበት እና ካህናትን የሚሾሙበት ሥርዓት ሁሉም የምስጢራተ ቤተክርስቲያን ጸሎቶች ለዚህ ምሳሌ ይሆናሉ። እነዚህ ሁሉ በሐዋርያት ዘመን ይሠሩባቸው የነበሩ ሥርዓቶች ሲሆኑ በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥም እየተሠራባቸው ናቸው ወደፊትም ለዘመናት ይቀጥላሉ።

እነዚህ ሥርዓቶች በጥንቷ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የኖሩ አሁንም ያሉ ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው።





# ምዕራፍ አምስት

## ኃጢአት የሚሠረይባት አንዲት ጥምቀት:

ጥምቀት አንድ አማኝ የቤተክርስቲያን አባል የሚሆንበት የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ምስጢር ነው። በጰራቅሊጦስ ዕለት አይሁድ ልባቸው ተነክቶ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት "ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?" አሏቸው። ጴጥሮስም "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" አላቸው። (ሐዋ 2:37፣38) ቃሉንም በስጦታ የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ (ሐዋ 2:41)። ሦስት ሺህ የሚያህል በአንድ ቀን ማጥመቅ ቀላል አልነበረም ነገር ግን ኃጢአት ይሰረይ ዘንድ ጥምቀት ጠቃሚ በመሆኑ ማጥመቁ አስፈላጊ ነበር።

ስለ ጥምቀት ጥቅም ማስረጃ የሚሆነን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ በተናገረው ቃል ውስጥ ይገኛል።

"እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" (ዮሐ 3:5)። ጥምቀት ለድኅነት አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ጌታችን ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ በተናገረው ቃል ውስጥ ተቀምጧል፤"ያመነ የተጠመቀም ይድናል"(ማር 16:16)።

በሐዋርያት ሥራ መፅሐፍ ውስጥ ጥምቀት ሁልጊዜ እምነትን ተከትሎ የሚፈፀም መሆኑ ተገልጿል።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም በጰራቅሊጦስ ዕለት (ሐዋ 2:41)፣ የሰማርያ ከተማ ባመነች ጊዜ (ሐዋ 8)፣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባመነ ጊዜ (ሐዋ8:36-37)፣ ቆርኔሌዎስና ከእርሱም ጋር የነበሩት ሰዎች ባመኑ ጊዜ (ሐዋ 10 :47-48)፣ ቀይ ሐር ሻጭ የነበረችው ልድያ ባመነች ጊዜ (ሐዋ 16:14-15)፣ የወሕኒው ጠባቂ ባመነ ጊዜ (ሐዋ 16:31-33) .....ወዘተ ተከስቷል። ጥምቀት ለኃጢአት ማስተሠሪያ እንደሚጠቅም የጠርሴሱ ሳውል የተለወጠበት ታሪክ ማስረጃ ነው።

ሳውል ወደ ደማስቆ ሲሄድ ጌታ ተገልጾ በአሕዛብ ፊት ስሙን ይሸከም ዘንድ ለእርሱ የተመረጠ ዕቃ አድርጎ ጠራው (ሐዋ 9:3-16) ። ከዚያም ሐናንያ የሚሉት የደማስቆ ሰው ለሳውል፤ "ወንድሜ ሳውል ሆይ... ለምን ትዘገያለህ? ተነሳና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትም ታጠብ አለው"(ሐዋ 22:16)።

ይህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተብሎ የተጠራው ታላቅ ሰው ከታላቁ ጥሪ ባሻገር ኃጢአቱን ለማጠብ መጠመቅ አስፈልጎት ነበር። ኃጢአቱ በመለኮታዊ ጥሪውም ሆነ እምነትን በመቀበሉ አልታጠበለትም ነበር።

ጥምቀት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል። (ገላ 3:27) ሲል የተናገረለት እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህ ማለት በጥምቀት አማካይነት በክርስቶስ ፅድቅ ማረፍ ማለት ነው። ይህም የሚሆነው ሐዋርያው፤ "በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ" (ቈላ 2:12) እንዳለው ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር መሞት እና ከእርሱም ጋር መነሳት እውነት በመሆኑ ነው። በዚህ አይነት መቀበር አሮጌው ሰዋችን



www.ethiopianorthodox.org



ከጌታችን ጋር ተሰቅሎ ሞቷል። (ሮሜ 6:6)። ሐዋርያው እንዳብራራው፤ "እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" (ሮሜ 6:4፤5)። ስለዚህ ጥምቀት ማለት ሞቶ አዲስ ልደት መቀበል ነው። ማለትም የአሮጌው ሰው መሞት እና ከክርስቶስ አምሳል በኋላ የአዲሱ ሰው መወለድ ነው ይህም ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ነው(ዮሐ 3:5)።

ሐዋርያው፤ "እንደምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን፤" (ቲቶ 3:5) እንዳለ። በዚህ አዲስ ልደት ከቅዱሳን አንዱ በአንድ ወቅት ቤተክርስቲያን እናትህ ከሆነች አባትህ እግዚአብሔር ብቻ ነው ሲሉ እንደተናገሩት የእግዚአብሔር እና የቤተክርስቲያን ልጆች እንሆናለን።

በጥምቀት የክርስቶስን ለይቅርታ የተከፈለ የደም ዋጋ እናገኛለን በዚህም ከጥምቀት በፊት የነበሩት ሁሉም ኃጢአቶች ይቅር ይባላሉና፤ ጥምቀት አይደገምም፣ጥምቀት አንዲት ናት። ከጥምቀት በኋላ የምንሠራቸው ግላዊ ኃጢአቶች ግን በምስጢረ ንስሐ ስርየት ያገኛሉ።

በጌታችን ቃል መሰረት (ዮሐ 3:5) ጥምቀት ኃጠአትን ለማስተሰረይ እና ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት እጅግ አስፈጊ ስለሆነ ልጆቻችንን እናጠምቃቸዋለን። ጌታችን "ያመነ የተጠመቀም ይድናል" (ማር 16:16) ሲል እንደተናገረው ጥምቀት እምነትን መቀበልን መከተል አለበት። ይህም

ተግባራዊ የሚሆነው ለአዋቂዎች ሲሆን ሕፃናት ግን በቤተሰቦቻቸው እምነት መሠረት ይጠመቃሉ።

## አንዲት ጥምቀት፡

ሐዋርያው፣ "አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ (ኤፌ 4፡5) ይላል። ጥምቀት አንዲት ናት ነገር ግን ቅድመ ሁኔታዎች አሉት።

1. አንድ የሚለው ዕምነትን የሚያውጅ ነው። ለዚህም ከእኛ ጋር በእምነት አንድ የሆኑትን የአብያተክርስቲያናት ጥምቀት እንቀበላለን፣
2. ለፍርድ፣ ተገዢ ባልሆነ በታወቀ ካህን መፈጸም አለበት። ይህ ህግ በ 276 ዓ.ም በቅዱስ ቆጵርያኖስ መሪነት በተካሄደው የካርቴጅ ጉባኤ ላይ የተደነገገ ነው።
3. ጥምቀት በትክክለኛ መንገድ መፈፀም አለበት፣ ተጠማቂውን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማድረግ መፈፀም አለበት።

ጥምቀት አንዲት በመሆኗ አንድ ሰው ከክርስትና ከወጣ በኋላ ወደ ክርስትናው ተመልሶ ቢመጣ አይደገምም።

## የሙታን መነሣት፡

በሙታን መነሣት እናምናለን በጻድቃንና ኃጥአን መነሣት እናምናለን።

በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል "በመቃብር ያሉ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት



ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ"(ዮሐ 5፤28-29) ተብሏልና።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የትንሣኤያችን በኩራት ነው። ለቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው መልዕክት ምዕራፍ 15 በዋናነት ስለሙታን መነሣት ይናገራል። ሐዋርያው፡ "አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ነገር ግን እንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደበኩራት ነው፣ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው።"

ቁሳዊ ባልሆነ መንፈሳዊና ሰማያዊ አካል እንነሣለን።

ስለሚነሳው አካል ሐዋርያው ሲናገር "በውርደት ይዘራል በክብር ይነሣል በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል ፍጥረታዊ አካል ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሣል ... የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን .. ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም" (1 ቆሮ 14፡42-50) አለ። ዳግመኛ "መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፣ እርሱም ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውንሥጋችንን ይለውጣል" (ፊል 3፡20-21) አለ። ይህ ማለት ጌታችን የተነሣበትን ክቡር ሥጋውን በሚመስል የከበረ ሥጋ እንነሣለን ማለት ነው።

በአጠቃላይ ትንሣኤ ጊዜ ፍርድ ይከናወናል፣ ይህም የሚሆነው በጌታችን ዳግም ምጽአት ነው። ስለዚህም ይህ ተጻፈ፡ ‹‹የሰው

www.ethiopianorthodox.org

ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለው ያን ጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል" (ማቴ 16፡27)፡፡ ዳግመኛም "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፡፡ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል፡፡" (ማቴ 25፡31-33)፡፡ ፍርዱም "እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ" (ማቴ 25፡46) በሚል ቃል ተጀምሮ ይጠናቀቃል፡፡

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍም ስለፍርድ ይናገራል፤ "ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ መጻሕፍትም ተከፈቱ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደነበር እንደሥራቸው መጠን ተከፈሉ፡፡ ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ እያንዳንዱም እንደሥራው መጠን ተከፈለ፡፡ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ፡፡ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው፡፡ በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣለ፡፡" (ራእ 20፡ 12-15)

በትንሣኤ ሕያዋን ሆነው የሚቀሩት ይነጠቃሉ አካላቸውም ይለወጣል፡፡

ያንቀላፉቱን ሐዋርያው በ(1 ተሰ 4፡14) እንደተናገረው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ከአእላፋት





ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል (ይሁ 14)፡፡ "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ ከዚያም በኋላ እኛ ህያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፡፡ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡" (1 ተሰ 4፡16፡17)

በትንሣኤ በደመና በምንነጠቅበት ወቅት በድንገት በመንፈሳዊ አካል እንለወጣለን፡፡ ሐዋርያው "ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋላኛው መለከት ሲነፋ ሁለችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፡፡ እኛም እንለወጣለን፡፡ ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና፡፡" (1 ቆሮ 15፡51-53) አለ፡፡ ይህ ማለት ለመበስበስ እና ለሞት ተገዢ ያልሆነውን መንፈሳዊና ሰማያዊ አካል እንለብሳለን ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ሦስት ዋና ዋና ሁነቶች ተከታትለው ይከናወናሉ፡ እነርሱም

1. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን መላእክቱ እና ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ዳግመኛ መምጣት፤
2. የሙታን መነሣት- የጻድቃንም የኃጥአንም መነሣት፤
3. ሐዋርያው "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በ!ሥጋው የሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል፡፡" (2 ቆሮ 5፡10) ሲል የተናገረለት አጠቃላይ ፍርድ ናቸው፡፡



www.ethiopianorthodox.org

እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ ይህ ዓለም ፍጻሜውን ያገኛል፤ የሚመጣው ዘላለማዊ ሕይወትም ይጀምራል ሁሉም እንደየሥራው ደረጃ ይኖራል።

<u>የዚህ ዓለም ፍፃሜ፣</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሰማይና ምድር ያልፋሉ (ማቴ 5፡18) ብሎ ተናግሯል። ታዲያ ባለራዕዩ ቅዱስ ዮሐንስ እንደተናገረው፣ "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ባሕርም ወደፊት የለም።" (ራዕ 21፡1)

"ታላቅ ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም።" (ራዕ 20፡11)

ስለዚህ ዓለም ፍጻሜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ተናግሯል፤

"የጌታው ቀን ግን እንደሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፤ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል።" (2 ጴጥ 3፡10)

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ከዓለም ፍጻሜ ጋር የተገናኙ ብዙ ነገሮችን በማብራራት ያስረዳል።

ለምሳሌ፣ ሰባቱን መለከት የያዙት ሰባቱ መላእክት ከነፉ በኋላ የተከሰቱት ሰባቱ መከራዎች (ራዕ 8) እንዲሁም በየድምጻቸው የተናገሩት ሰባቱ ነጎድጓድ (ራዕ 10፡ 3፡4)

ጌታችን ምጽአቱን ቀድመው ስለሚታዩት ምልክቶች እንዲህ በማለት





ገልጸአል።

"ከዚህ ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ" (ማቴ 24፡29)። በራእየ ዮሐንስም ውስጥ ሰባተኛው ማህተም በተፈታ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር ተከስቶአል (ራዕ 6፡12-16)

<u>የሚመጣው ሕይወት፣</u>

በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆናል የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው። (1 ቆሮ 15፡ 24-28)።

የሚመጣው ዓለም ሕይወት የሚጀመረው እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በሚያድርባት በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ነው። (ራእይ 21፤ 2፡3) በገነት የቆዩ ጻድቃንም ወደዚህች ከተማ ገብተው ይኖራሉ።

ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ኃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና፤ በዙፋንም የተቀመጠው "እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ" ብሏልና (ራዕ 21፡ 4፡5)።

ለሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለሆነ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም። በዚያም ሌሊት የለም፣ ለበጉም በሆነው በሕይወት



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም (ራዕ 21፥23-27)

ጻድቃን ጌታችን ድል ለነሱት በገባው ቃልኪዳን እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው "ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው" ተብሎ በተነገረው ደስ ይላቸዋል፡፡ (1ቆሮ 2፥9)

የሚመጣው ዓለም ሕይወት ዘላለማዊ የደስታ ሕይወት ያለበት ነው ጻድቃን በትንሣኤ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉና (ማቴ 22፥30)፡፡ እግዚአብሔር ደስታቸው ይሆናል፤ "ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል ... ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ" (ራእ 22፥ 4፥5)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው "ዛሬስ በመስተዋት እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ" (1ቆሮ 13፥12)፡፡

የሚመጣውን ዓለም ሕይወት ማብራራት ለእኛ የሚቻል ወይም ቀላል አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን፤ ወደ ገነት በተነጠቀ ጊዜ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማሁ አለ (2ቆሮ 12፥4)፡፡ ታዲያ ስለዘላለማዊ ደስታ ምን ማለት ይቻላል? ከላይ የተለገጡትን ሁሉ እንዴት መረዳትስ ይቻላል?!



www.ethiopianorthodox.org